ኢፕድ
# አዲስ ዘመን
ዓርብ
82ኛ ዓመት ቁጥር 146 ጥር 26 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



# «በአዲስ ሃሳብ ተስፋ ሰንቆ በመነሳት ለለውጥ መትጋት ያስፈልጋል»

-ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር)

ዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- የትናንት ስህተት የፈጠረውን ስብራት በመረዳት ለመፍትሔው በአዲስ ሃሳብ እና ጉልበት ተስፋ ሰንቆ በመነሳት ለለውጥ መትጋት እንደሚገባ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በማኅበራዊ ትስስር ገጻቸው "የትናንት ዘር፣ የዛሬ ፍሬ፣ የነገ ስንቅ!" በሚል ርዕስ ባስተላለፉት መልዕክት፤ እንደ ሀገርና ማኅበረሰብ ለላቀ ለውጥና ነገን የተሻለ ለማድረግ መትጋት እንደሚገባ አመልክተዋል።

ችግሮች ሲገጥሙ ጣት መጠቆምና በቀዳዳ ሾልኮ ማምለጥ የሞኞችና የፈሪዎች መፍትሔ መሆኑን በመጠቆምም፤ ትክክለኛው የብልህና የጀግኖች መንገድ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ፊት ለፊት ተጋፍጦ በጥበብ ለመርታት መፍጨርጨር መሆኑንም ገልጸዋል።

«በአዲስ ሃሳብ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የኛ ባልሆነ ጥፋት ላልተገባ ቅጣት ተዳርገናል ሲሉ ግብር ከፋዮች ተናገሩ

- ከአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ምላሽ ለማግኘት ያደረግነው ሙከራ አልተሳካም

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ራሱ በፈጠረው ችግር ያልተገባ ቅጣት እንደጣለባቸው ንግድ ፍቃድ ለማሳደስ የሄዱ ነጋዴዎች ተናገሩ። የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ንግድ ጽሕፈት ቤት ከበላይ አካላት በተሰጠው መመሪያ መሠረት እንደሠራ ሲገልጽ ጉዳዩን በተመለከተ የአዲስ አበባ ከተማ ንግድ ቢሮ በተደጋጋሚ ላቀረብንለት ጥያቄ ምላሽ ሊሰጠን አልቻለም።

በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የደረጃ 'ሐ' ንግድ ፈቃድ ለማሳደስ ወደወረዳው ንግድ ጽሕፈት ቤት መሄዳቸውን የሚናገሩት አቶ ሃብታሙ በለጠ (ስማቸው የተቀየረ) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ራሱ በፈጠረው ችግር ላልተገባ ቅጣት መዳረጋቸው ኢ-ፍትሐዊ ነው።

አንድ ንግድ ፈቃድ ለማደስ የሚሄድ ተገልጋይ ከነጋዴው የሚጠበቅበትን መስፈርት ሁሉ አሟልቶ ለመስተናገድ ከሄደ ተራውን ጠብቆና በአግባቡ ተስተናግዶ መውጣት አለበት። ነገር ግን እሳቸው ምንም ባላጠፉት ምክንያት ላልተገባ ቅጣት መዳረጋቸው ተገቢ

የኛ ባልሆነ ጥፋት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በግማሽ ዓመት 13 ቢሊዮን ብር አተረፈ

- የባንኩ ጠቅላላ ሀብት 1 ነጥብ 2 ትሪሊዮን ብር ደርሷል
- በዲጂታል አማራጮች ከአንድ ትሪሊዮን ብር በላይ ክፍያዎችን ፈጽሟል

ዳግማዊት አበበ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በ2015 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ግማሽ ዓመት ውስጥ 13 ቢሊዮን ብር ማትረፉን አስታወቀ። የባንኩ ጠቅላላ ሃብት 1 ነጥብ 2 ትሪሊዮን ብር መድረሱንም ጠቁሟል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በትናንትናው ዕለት የ2015 ግማሽ የበጀት ዓመት የሥራ አፈፃፀም ግምገማ ጉባዔ ባካሄደበት ወቅት የባንኩ ፕሬዚዳንት አቶ አቤ ሳኖ እንደተናገሩት፤ ባንኩ በ2015 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ግማሽ ዓመት ውስጥ 13 ቢሊዮን ብር አትርፏል።

ባንኩ ባለፉት ስድስት ወራት ሁለት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ለሚሆኑ አዲስ ደንበኞች የቁጠባ ሂሳብ መክፈቱን የገለጹት ፕሬዚዳንቱ፤ የባንኩ የደንበኞች ብዛት 38 ነጥብ አንድ ሚሊዮን ደርሷል ብለዋል።

በተጨማሪም የባንኩን የቅርንጫፍ አገልግሎት ለማስፋት በተከናወኑ ሥራዎች 55 አዳዲስ ቅርንጫፎች የተከፈቱ ሲሆን በዚህም ባንኩ የቅርንጫፍ ቁጥሩን አንድ ሺህ 879 አድርሷል ሲሉ ገልጸዋል።

በአጠቃላይም በስድስት ወራት ውስጥ በተሠሩ ሥራዎች 13 ቢሊዮን ብር ማትረፉን ተናግረው፤ በዲጂታል አማካኝነት የሚፈጸመው ክፍያም ከአንድ ነጥብ ሦስት ትሪሊዮን ብር በላይ መድረሱን ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለደንበኞቹ ያልተቋረጠ



አቶ አቤ ሳኖ

የባንክ አገልግሎት ለማቅረብ የዲጂታል እና የካርድ የባንክ አገልግሎቶችን እያስፋፋ እንደሚገኝ ገልጸው፤ ባለፉት ስድስት ወራት የካርድ ተጠቃሚዎችን ከሁለት ነጥብ 32 ሚሊዮን ወደ 8 ነጥብ 8 ሚሊዮን፤ የሞባይል ባንኪንግ ተጠቃሚዎችን ከሦስት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ወደ ስድስት ሚሊዮን እንዲሁም የኢንተርኔት ባንኪንግ ተጠቃሚዎችን ከ 17 ሺህ 145 ወደ 39 ሺህ 865 አሳድጓል ብለዋል።

አራት ነጥብ አራት ሚሊዮን አዳዲስ የሲቢኢ ተጠቃሚዎችን በመመልመል አጠቃላይ የሲቢኢ ብር

የኢትዮጵያ ንግድ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡ ገበቦ ገብሬ

አቶ ሰለሞን ሶካ

# ባለፉት ስድስት ወራት 2 ሺህ 49 የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች ከሽፈዋል

- በጥቃቱ ሊደርስ የነበረ የ15 ቢሊዮን ብር ኪሳራ ድኗል

ሄለን ወንድምነው

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ስድስት ወራት 2 ሺህ 49 የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች እንዲከሽፉ መደረጉን የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር አስታወቀ።

ባለፉት ስድስት ወራት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር
ደርባ ሲሚንቶ DERBA CEMENT

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ

ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)
የሁሉም ባንክ
Bank for all !
የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ !
በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።
Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia









ቴክኖሎጂን የሚጠቀም ዘመን ተሻጋሪ ሠራዊት ለማፍራት በጥናት መደገፍ ይገባል

ገጽ 3

# በዓሉ ለከተማዋ የቱሪዝም መነቃቃት ትልቅ አስተዋፅዖ አለው

ማሕሌት ብዙነህ



አዲስ አበባ ፡ በደብረታቦር ከተማ የሚከበረው የቅዱስ መርቆሪዮስ ዓመታዊ በዓል እና የፈረስ ጉግስ ጨዋታ በዓል ለከተማዋ ቱሪዝም መነቃቃት ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንዳለው የደብረታቦር ከተማ ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ ገለጸ።

የደብረታቦር ከተማ አስተዳደር ባሕልና ቱሪዝም ኃላፊ አቶ ጌትነት ከፌ ለኢትዮጵያ ፕሬስ እንደገለጹት፤ ከ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ይዘቱን ጠብቆ በየዓመቱ ጥር 25 ቀን በአጅባር ሜዳ ይከበራል። በዓሉ ከተማዋ ሰፊ የሆነ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ እና የቱሪስት መዳረሻ እንድትሆን ስለሚረዳ የብርሀን ከተማ የሚል ስያሜ እንዲኖራት አድርጓታል ብለዋል።

የዘንድሮ ክብረ በዓሉ የፌዴራል እና የክልል መንግሥታት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች፣የሃይማኖት አባቶች ፣ከተለያዩ ወረዳዎች እና አካባቢዎች ተሰባስበው የሚመጡ ፈረሰኞች እና ምዕመናን በተገኙበት ተከብራል ተብሏል።

ከተማ አስተዳደሩ የዘንድሮን በዓል ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ሕዝባዊ በዓል በማድረግ እና ኅብረተሰቡን በማሳተፍ የተሻለ ሥራ ሠርቷል። በቱሪዝሙ ዘርፍ ወደ 10 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ ሊገኝ እንደሚችልም ተናግረዋል።

ይህንን ከፍተኛ የሆነ የቱሪዝም እንቅስቃሴ በማድረግ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከ25 ዓመት በፊት ተቋርጦ የነበረውን በረራ በይፋ እንደጀመረ ኃላፊው አውስተዋል።

እንደ አቶ ጌትነት ማብራሪያ፣ ከተማዋ ከ1327 ጀምሮ የተቆረቆረች እና በውስጥዋ ከአምስት በላይ ቤተመንግሥት እንዲሁም ጥንታዊ እና ታሪካዊ ቅርሶች ያሉባት የታሪክ ከተማ ናት። ከተማ አስተዳደሩ የከተማዋ ባሕላዊ እሴት ጠብቆ ለትውልድ ለማስተላለፍ ጥለታዊ የሆኑ አልባሳት፣ ጋሻ፣ ለምድ የመሳሰሉ ቁሳቁሶችን በማቅረብ እና በማስተላለፍ ጉልህ ሚና እየተጫወተ ነው።

በዓሉ ከተለያዩ የሀገር ክፍሎች ጎብኚዎችን በመሳብ የቱሪስት ማዕከል ፣ ለአካባቢው የሥራ ዕድል ፣ለሆቴል አገልግሎቶች እና ለንግዱ ዘርፍ መነቃቃት እና የገቢ ምንጭ ይፈጥራል ብለዋል።

የደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ የታሪክ እና ቅርስ መምህር እና የአለቃ ገብረሐና ባሕል ጥናት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር መምህር መሰረት ወርቁ እንደገለጹት፤ ይህ ሀይማኖታዊ እና ባህላዊ ይዘት ያለው በዓል ሲሆን ለከተማዋ እድገት እና ኢንቨስትመንት ፍሰት ትልቅ ሚና አለው።

ዩኒቨርሲቲው በዳይሬክተር ደረጃ የባሕል ማዕከል በማቋቋም የመርቆርዮስን በዓልን ጨምሮ በከተማው ያሉ ቅርሶችን በማጥናት እና በማስተዋወቅ ብሎም ለትውልድ ለማስተላለፍ እየሠራ መሆኑንም አመልክተዋል።

መምህር መሠረት እንደተናገሩት ይህ የፈረስ ጉግስ ጨዋታ ክርስትና ከገባ ጀምሮ ያለ ጥንታዊ ባህል ሲሆን የደብረታቦር ዩኒቨርሲቲ የታሪክ እና ቅርስ ትምህርት ክፍል ፣ የአለቃ ገብረሐና ባህልና ጥናት ማዕከል ከስፖርት ሳይንስ ትምህርት ክፍል ጋር እንዲሁም ከከተማው ባሕልና ቱሪዝም ጋር በመተባበር ከማይዳሰሱ ቅርሶች ውስጥ በዩኔስኮ ለማስመዝገብ እየተሠራ ነው ብለዋል።

በዓሉ ታሪካዊ ይዘቱን ይዞ እንዲቆይ ለተሳታፊዎች የተለያየ ስልጠና እና ድጋፍ እያደረጉ መሆናቸውንም ገልጸዋል።




አቶ ሙሉጌታ አያሌው

# ከሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ለያዙ መዝገቦች ውሳኔ ተሰጥቷል

ሙሳ ሙሐመድ

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ከሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ለያዙ መዝገቦች የፌዴራል ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ውሳኔ መሰጠቱን አስታወቀ።

የፌዴራል ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን (ፌታይኮ) ፕሬዚዳንት አቶ ሙሉጌታ አያሌው እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ ከ2 ቢሊዮን ብር በላይ ለያዙ መዝገቦች በተያዘው በጀት ዓመት የግማሽ ዓመት ውስጥ ውሳኔ ተሰጥቷል።

በግማሽ ዓመቱ 654 የይግባኝ መዛግብት ቀርበው እንደነበር ፕሬዚዳንቱ ጠቅሰው፣ ከቀረቡት ውስጥ በ320 መዛግብት ላይ የቃል ክርክር በማድረግ ለውሳኔ ተቀጥረዋል ብለዋል።

በ316 መዛግብት ላይ ውሳኔ መሰጠቱን የተናገሩት ፕሬዚዳንቱ፣ የተቋሙ ውሳኔ የመስጠት አቅምም 98 ነጥብ 7 በመቶ ደርሷል። ከባለፈው ዓመት የስድስት ወር አፈፃፀም ጋር ሲነፃፀር መሻሻል አሳይቷል ብለዋል።

የይግባኝ ቅሬታዎችን በሕግና በአሠራር በመመርመር ጥራት ያለው ውሳኔ የመስጠት አቅም መቶ በመቶ ለማድረስ እየተሠራ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፣ አሁን ላይ ፌታይኮ ተቋማዊ የውሳኔ መስጠት አቅሙ 98 ነጥብ 7 በመቶ መድረሱን ገልጸዋል።

ፕሬዚዳንቱ አክለውም የቅሬታ መዛግብት ብዛትና ከያዙትን የገንዘብ መጠን አኳያ ከገቢዎች 107 መዛግብትና የያዙት የገንዘብ መጠን አንድ ቢሊዮን 223 ሚሊዮን 541 ሺህ 270 ነጥብ 56 ብር እንደሆነ ተናግረዋል።

በተመሳሳይ ከጉምሩክ 209 መዛግብት ቀርበዋል፣ የያዙት የገንዘብ መጠንም 891 ሚሊዮን 252 ሺህ 582 ነጥብ 88 መሆኑን አመላክተው፣ በጥቅሉ በ316 መዛግብትና በግማሽ ዓመቱ ውስጥ የ2 ቢሊዮን 114 ሚሊዮን 793 ሺህ 853 ነጥብ 44 ብር ያያዙ መዛግብት ውሳኔ መስጠቱን ፕሬዚዳንቱ ገልፀዋል። ይህም ከባለፈው በጀት ተመሳሳይ ወር ጋር ሲነፃፀር በ9 መዛግብት ብልጫ አሳይቷል ብለዋል።

የኮሚሽኑ የፕላንና ለውጥ ማስተባበሪያ ዳይሬክተር አቶ እዮብ አለማየሁ እንደገለጹት፤ የተገልጋዮችን እርካታ ለማሳደግ አገልግሎት ካገኙት 1127 ተገልጋዮች ውስጥ 1086 በተሰጣቸው አገልግሎት መርካታቸውን ገልጸዋል። 41 ደግሞ ተገልጋዮች በተሰጣቸው ግልጋሎት አለመርካታቸውን የጠቀሱ ሲሆን፣ የተቋሙ የተገልጋይ እርካታ ደረጃ 96 ነጥብ 8 በመቶ ደርሷል ብለዋል።

ዳይሬክተሩ አክለውም፣ ተቋማዊ የአገልግሎት አሰጣጡን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተደራሽ ለማድረግ ሲስተም የማልማት ሥራው ሙሉ በሙሉ ተጠናቆ ለተገልጋዩ ምቹ ሆኖ ሥራ ላይ ውሏል ብለዋል።

በግማሽ ዓመቱ 250 ተገልጋዮች በቀጥታ በኦንላይን ምዝገባ አካሂደዋል፤ ተቋማዊ የአገልግሎት አሰጣጡን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ለመደገፍ ከ2011-2014 ዓ.ም ጀምሮ በሀርድ ኮፒ ከቀረቡ መዛግብት ውስጥ 1885ቱን ዲጂታላይዝ ማድረግ መቻሉን ገልፀዋል።

# የግብር ክፍያዎችን በቴሌ ብር ለመሰብሰብ የሚያስችል ስምምነት ተፈረመ

አስናቀ ፀጋዬ




ፎቶ፡ ሃዲስ አብርሃ

አዲስ አበባ፡- የግብር ክፍያዎችን በቴሌ ብር አማካኝነት ለመሰብሰብ የሚያስችል የአጋርነት ስምምነት በኢትዮ ቴሌኮምና በገቢዎች ሚኒስቴር መካከል ተፈረመ።

ስምምነቱ በተፈረመበት ወቅት የኢትዮ ቴሌኮም ሞባይል ቢዝነስ ዲቪዥን ዋና ኦፊሰር አቶ ብሩክ አድሃኖም እንደተናገሩት ስምምነቱ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ደንበኞች የተለያዩ የግብር ክፍያዎችን ቀላል፣ ፈጣን፣ ምቹና አስተማማኝ የሆነውን ቴሌ ብር የዲጂታል ክፍያ ሥርዓትን ተጠቅመው በየትኛውም ጊዜና ቦታ የግብር ክፍያቸውን ያለምንም ውጣውረድ እንዲከፍሉ ያስችላቸዋል።

በዋናነትም ስምምነቱ የገቢዎች ሚኒስቴር የገቢ ግብርንና የግል ሠራተኞች የጡረታ መዋጮ፣የፌደራል ታክስ ክፍያዎችን በወቅቱ ለመሰብሰብና ለማሳለጥ ጉልህ ሚና እንደሚኖረውም ኦፊሰሩ ገልጸዋል።

በየጊዜው እያደገ የመጣውን የግብር ከፋዮች የክፍያ አማራጭ ፍላጎት ቀላልና አስተማማኝ በማድረግ የቴሌ ብር ተጠቃሚዎች ከግል ወይም ከድርጅት የቴሌ ብር አካውንታቸው በቴሌ ብር የሞባይል መተግበሪያ ወይም በአጭር ቁጥር *127# በመጠቀም የግብር ክፍያቸውን ባሉበት ቦታ ሆነው በቀላሉ መክፈል የሚያስችላቸው መሆኑንም ጠቁመዋል።

በቴሌ ብር ግብይት የሚፈጽሙ ነጋዴዎች ከሚፈጽሟቸው ግብይቶች ከሰበሰቡት ገንዘብ ላይ ለግብር ክፍያ በቀጥታ መክፈል የሚችሉበት ሁኔታ እንደተመቻቸላቸውም ዋና ኦፊሰሩ አያይዘው ጠቅሰዋል።

በተጨማሪም በቴሌ ብርና በገቢዎች ሚኒስቴር የሲስተም ትስስር አማካኝነት የደምበኞች የክፍያ ሁኔታን ወቅታዊ ለማድረግ ክፍያው እንደተፈፀመ ለደምበኛው የክፍያ ክሊራንስና ደረሰኝ በወቅቱ ለመስጠት በገቢዎች ሚኒስቴር ሰርቨር ላይ መረጃን ወቅታዊ በማድረግ በመዘግየት ምክንያት በግብር ከፋዩ ላይ የሚደርሰውን ቅጣት በማስቀረት ረገድ ስምምነቱ ትልቅ ፋይዳ እንዳለውም አስታውቀዋል።

አገልግሎቱን ለማግኘት የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ደንበኞች ወደ www.mor.gov.et በመግባትና የኤሌክትሮኒክ ታክስ አገልግሎት የሚለውን በመምረጥ፤ አስፈላጊውን ሂደት ሲጨርሱ ከገቢዎች ሚኒስቴር የሚሰጣቸውን የሰነድ ቁጥር በመጠቀም በቀላሉ ክፍያቸውን በቴሌ ብር መተግበሪያ ወይም በአጭር ቁጥር *127# በመጠቀም የግብር ክፍያ የሚለውን በመምረጥ ክፍያቸውን ፈፅመው ደረሰኝ ወዲያውኑ በኢ-ሜል አድራሻቸው ማግኘት እንደሚችሉም ዋና ኦፊሰሩ ጠቁመዋል።

በዚሁ ሁነት ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር ወይዘሮ ዓይናለም ንጉሴ ባለፉት የለውጥ ዓመታት ለግብር ከፋዮች የሚመጥናቸውን የሰለጠነ አገልግሎት መስጠት እንዲቻል የገቢዎች ሚኒስቴር በርካታ ሥራዎችን ሲሠራ መቆየቱን ገልፀዋል።

በተለይ ደግሞ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሀገር ውስጥ ግብርን በመሰብሰብ ሂደት ውስጥም ሆነ የውጪ ቀረጥና ታክስን ለመሰብሰብ ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ የተለያዩ የቴክኖሎጂ አማራጮችን በማልማት ተግባራዊ ሲያደርግ መቆየቱንም ሚኒስትሯ አስታውሰዋል።

«ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቶ የወረቀት አልባ አገልግሎትን እውን ማድረግና በተቋሙ ልህቀት ያለው አገልግሎት መስጠት» በሚል ሀሳብ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከፍተኛ ርብርብ እያደረገ እንደሚገኝም ጠቁመዋል።

በዚህም በርካታ ግብር ከፋዮች ከአስራ ሰባት ባንኮች ጋር እየሠሩ እንደሚገኙና የውጪ ቀረጥና ታክስ አከፋፈል ሥርዓትን ዲጂታላይዝ በማድረግ ተጨማሪ አዳዲስ አሠራሮችን ተቋሙ እያበለፀገ መሆኑንም ጠቅሰዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር ያደረገው ስምምነት ደግሞ እስካሁን ሲያደርግ የነበረውን ጥረት የበለጠ የሚያጠናክርና በዚሁ አማራጭ ብቻ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በዓመቱ ለመሰብሰብ ካቀደው 450 ቢሊዮን ብር ውስጥ በቀሩት ጊዜያት 70 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ እቅድ መያዙን አመልክተዋል።

በሂደት ሲስተሙን ለግብር ከፋዮች በማስፋት፣ በማስተዋወቅና በማስተማር ሁሉም የግብር አሰባሰብ በዚሁ ሥርዓት ውስጥ እንዲገባ ማድረግ የገቢዎች ሚኒስቴር ፍላጎት መሆኑን ጠቅሰዋል።

የቴሌ ብር አማራጭ ግብር ክፍያን ተግባራዊ ለማድረግም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ባሉት 11 ቅርንጫፎች ከከፍተኛ ግብር ከፋይ ጀምሮ እስከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ድረስ ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በንግድ ባንክ የቴሌ ብር አካውንቶች መከፈታቸውንም ሚኒስትሯ አብራርተዋል። ሥርዓቱ ጤንነቱ የተጠበቀ እንዲሆንም ከፍተኛ ጥንቃቄ ተደርጎ ሲሠራ እንዲቆይ መደረጉንም ሚኒስትሯ ተናግረዋል።

በዚሁ ሥርዓት ከየካቲት 1 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ወቅታዊ ግብር እንደሚሰበሰብና ከወቅታዊ ግብር ባሻገር ግን የውዝፍ እዳዎችና ሌሎችም የገቢ አማራጮችን ወደዚህ ሥርዓት የማስገባት ሥራ በቀጣይ እንደሚሠራ ገልፀዋል።

ቴክኖሎጂ ሁሌም መሻሻልን የሚፈልግ እንደመሆኑ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በአሁኑ ወቅት ለግብር አሰባሰቡ እየተጠቀመበት ያለውን «ሲክታክስ» የተሰኘውን መተግበሪያ በቀጣይ አሻሽሎ ይበልጥ አገልግሎቱን ቀልጣፋ፣ ተደራሽ፣ አስተማማኝና አርኪ ለማድረግ እየሠራ እንደሚገኝ ሚኒስትሯ አመልክተዋል።

# ቴክኖሎጂን የሚጠቀም ዘመን ተሻጋሪ ሠራዊት ለማፍራት በጥናት መደገፍ ይገባል

**ሞገስ ተስፋ**


ፎቶ፡ ኤዮብ ተፈሪ

አዲስ አበባ፡- ዘመናዊ ቴክኖሎጂን የሚጠቀም ጠንካራና ዘመን ተሻጋሪ ሠራዊት ለማፍራት ወቅቱን በዋጀ ጥናትና ምርምር መደገፍ እንደሚገባ ተገለጸ። አሁናዊና የወደፊቱ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ወታደራዊ ሙያ ላይ ያተኮረ የፓናል ውይይት በመከላከያ አዛዥነትና ስታፍ ኮሌጅ ተካሂዷል።

በመከላከያ አዛዥነትና ስታፍ ኮሌጅ በወታደራዊ ሙያ ላይ ያተኮረ የፓናል ውይይት በትናትናው ዕለት በተካሄደበት ወቅት የመከላከያ ሚኒስትር የፋይናንስ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ማርታ ሉዊጂ እንደተናገሩት፣ ከለውጡ ወዲህ በኢትዮጵያ በሪፎርም አመርቂ ውጤት ከተመዘገበባቸው ተቋማት ውስጥ የመከላከያ ሠራዊት አንዱ ነው። ከለውጡ በፊት በተቋሙ ይስተዋል የነበረውን ሁለንተናዊ መዛነፍ በሪፎርም ለማስተካከል ብዙ ሥራ ተሠርቷል፣ እየተሠራም ነው ብለዋል።

በየጊዜው እየተወሳሰበ ካለው የደህንነት ስጋት ለመላቀቅ ብሎም የአገሪቱን ሉዓላዊነት እና የሕዝቡን ደህንነት አስተማማኝ ደረጃ ላይ ለማድረስ በትኩረት እየተሠራ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ዘላቂ ሰላምና ዲሞክራሲን ማረጋገጥ የሚቻለው ጠንካራ የመከላከያ ሠራዊትና ጠንካራ ተቋም መገንባት ሲቻል ነው ብለዋል።

የሀገሪቱን አንድነት፣ ሰላምና ሉዓላዊነት የማይሹ ኃይሎች በተለይ የሀገር ውስጥ ተላላኪዎችን በመጠቀም መንግሥት በልማት ሥራዎች ላይ እንዳያተኩር የሚሠሩ በርካቶች ናቸው ያሉት ወይዘሮ ማርታ፤ ይህ ፍላጎት ሕዝቡ ሁልጊዜም በተመጽዋችነት እንዲኖር በማድረግ በፍላጎታቸው ብቻ እየተመራ ጉዳይ አስፈጻሚያቸው እንዲሆን ማድረግን ዓላማ ያደረገ መሆኑን አብራርተዋል።

ኢትዮጵያ የምትገኝበት የአፍሪካ ቀንድ፣ የኃያላን ሀገራት ትኩረት በመሳቡ ምክንያት የሀገሪቱ የደህንነት ስጋት ምንጭ መሆኑን የጠቆሙት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ በመሆኑም በቴክኖሎጂ እውቀትና ክህሎት የተካነ ብቁ ሠራዊት መገንባት ትልቅ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ መሆኑን አስምረውበታል።

የሀገራችንን ሰላም፣ ደህንነትና ሉዓላዊነት ማስከበር የሚቻለው ብቁ፣ ዘመኑን የሚመጥን ዘመናዊ ቴክኖሎጂን የሚጠቀም የሀገር መከላከያ ሠራዊት መገንባት ሲቻል ነው። ለዚህ ደግሞ በጥናትና ምርምር የተደገፈና በትምህርትና ስልጠና ብቁ የሆነ ሠራዊት መገንባት እንደሚገባ ሚኒስትር ዴኤታዋ ገልጸዋል።

ወይዘሮ ማርታ፣ ወቅቱን ያገናዘበና በቴክኖሎጂ የታነጸ ጠንካራ መከላከያ ሠራዊት ግንባታ እውን የሚሆነው የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የተሰጣቸውን ተልዕኮ በአግባቡ በመወጣት አስፈላጊውን ጥናትና ምርምር በማድረግ በውይይት አስደግፈው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ሲሠሩ ነው ብለዋል።

የመከላከያ አዛዥነትና ስታፍ ኮሌጅ ዋና አዛዥ ኮሎኔል ደመቀ መንግሥቱ በበኩላቸው፣ ኮሌጁ ከተመሠረተበት ከ1998 ጀምሮ በአራት የትምህርትና የሥልጠና ፕሮግራሞች ከፍተኛ መኮንኖችን ለግዳጅ ብቁ ማድረጉን ገልጸው፤ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ የሚጠቀም ጠንካራ ሠራዊት ሊኖር የሚችለው ወቅቱን በዋጀ ጥናትና ምርምር የተደገፈ ሠራዊት ሲኖር እንደሆነ በመገንዘብ እየተሠራ ነው ብለዋል።

ኮሌጁ የአመራር ክፍተትን ለመሙላት በርካታ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊትና የጐረቤት ሀገራት ከፍተኛ መኮንኖችን ተቀብሎ በአዛዥነትና ስታፍ ኮሌጅ በኮርስ ደረጃ በማስተማርና በማሰልጠን በሠራዊት ግንባታ ላይ የድርሻውን እየተወጣ እንደሚገኝም አክለው ተናግረዋል።

እንደ ኮሎኔሉ ገለጻ፤ ስታፍ ኮሌጁ በመጀመሪያ ዲግሪ፣ በሁለተኛ ዲግሪ በዲፕሎማና በአጫጭር ስልጠናዎች አንድ ሺ 97 ከፍተኛ መኮንኖችን ያስመረቀ ሲሆን 982ቱ ኢትዮጵያውያን፤115ቱ የጎረቤት ሀገራት ዜጎች ናቸው። የማስተማር ሂደቱን ለማዘመን ሀገራዊ፣ ቀጠናዊና ዓለማቀፋዊ የደህንነት ሁኔታን በማገናዘብ በምርምር የተደገፈ ሥራ እየተሠራ ነው፡ ፡የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሙ ከንዑስ ቡድን አስተሳሰብ ነጻ በመሆንና ሙያዊ አስተሳሰብን በመገንባት ዘመን ተሻጋሪ ተቋማዊ ማንነትን መፍጠር ዓላማ ያደረገ መሆኑም በዚሁ ወቅት ተገልጿል።

# በአፋርና አማራ ክልሎች በጦርነቱ የወደሙ 71 ትምህርት ቤቶች ግንባታ በዚህ ዓመት ይጠናቀቃል

**ጽጌረዳ ጫንያለው**


ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ

አዲስ አበባ፡- በአማራና በአፋር ክልሎች ሙሉ ለሙሉ በጦርነቱ የወደሙ 71 ትምህርት ቤቶች በዚህ ዓመት ግንባታቸው ተጠናቆ በሚቀጥለው የትምህርት ዘመን ወደ አገልግሎት እንደሚገቡ ትምህርት ሚኒስቴር አስታወቀ። ለዚህም 55 የሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች ተመርጠው ወደ ሥራ መግባታቸውንና የግንባታ ግብዓት ለግንባታው መጓተት እንቅፋት እንዳይሆን ግዢ እየተፈጸመ መሆኑን ጠቁሟል።

በትምህርት ቤቶቹ ግንባታ ዙሪያ ከግንባታ አማካሪዎችና ተቋራጮች ጋር በተደረገው የውይይት መድረክ ላይ የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ እንደተናገሩት፤ ሁሉም ትምህርት ቤቶች ግንባታቸው በዚህ ዓመት ይጠናቀቃሉ።

ትምህርት ቤቶቹ ለ2016ዓ.ም የትምህርት ዘመን መድረስ ይኖርባቸዋል ያሉት ፕሮፌሰር ብርሃኑ፤ ስለሆነም ትምህርት ሚኒስቴር ብቻ ሳይሆን ሀገር አምኖባችሁ የተመረጣችሁ ሥራ ተቋራጮች ኃላፊነታችሁን በሚገባ መወጣት ይኖርባችኋል ብለዋል። በእያንዳንዱ ሥራ ላይ የሚወጡ ወጪዎች ታውቀው ወደሥራ ስለሚገባ ችግር እንደማያጋጥምም ፕሮፌሰር ብርሃኑ ተናግረዋል።

የግንባታ ግብዓት ለግንባታው መጓተት እንቅፋት እንዳይሆን ትምህርት ሚኒስቴር ኃላፊነቱን ወስዶ ግዢ ፈጽሟልና በተሰጣችሁ ልክ መሥራትና ማስረከብ ይኖርባችኋል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ለትምህርት ቤቱ የሚያስፈልገው የሲሚንቶና የብረት መጠንን በተመለከተ ከኢትዮጵያ አርክቴክቶች ማኅበር ጋር በመሆን ስለተሠራ ለኮንትራክተሩ የሚሰጠው በልኬት ይሆናል ብለዋል። ይህ ደግሞ የሀብት ብክነትን ለመቆጣጠር እንደሚያስችል ተናግረዋል።

ትምህርት ቤቶቹን ለመገንባት የሚያስችል 2 ነጥብ 8 ቢሊዮን ብር ማሰባሰብ እንደተቻለ የገለጹት ሚኒስትሩ፤ ከ71 ትምህርት ቤቶች ውስጥ 50 ትምህርት ቤቶች የሚገነቡት በትምህርት ሚኒስቴር ወጪ ሲሆን፤ አምስት ትምህርት ቤቶች ደግሞ ከዲያስፖራ ትረስት ፈንድ በተገኘ ገንዘብ ይሆናል ሲሉም ተናግረዋል። ቀሪዎቹ 16 ትምህርት ቤቶች በሰዎች ለሰዎች ድርጅት የሚገነቡ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥም ስምንቱ በአፋር ክልል፣ ሶስቱ በአማራ ክልል እና ቀሪዎቹ አምስቱ ደግሞ በሌሎች ክልሎች የሚገነቡ ናቸው ተብሏል።

በጦርነቱ በአጠቃላይ 3ሺህ 300 ትምህርት ቤቶች ሙሉ ለሙሉ የወደሙ ሲሆን፤ አንድ ሺህ 65ቱ አማራ ክልል፣ 95 የሚሆኑት ደግሞ አፋር ክልል የሚገኙ መሆናቸው ተገልጿል።


አምባሳደር ብርቱካን አያና

# በ36ተኛው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ ሆቴሎች እንግዶችን በመቀበል ልዩ ኃላፊነት አለባቸው

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ ለሚካሄደው 36ተኛው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ ሆቴሎች እንግዶችን በመቀበል ልዩ ኃላፊነት እንዳለባቸው ተገለጸ። በቱሪዝም ሚኒስቴር አዘጋጅነት ለጉባኤው መደረግ ባለበት ዝግጅት ዙሪያ ትናንት ውይይት ተካሂዷል ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ብርቱካን አያና በዚሁ ወቅት እንደተናገሩት፤ ለጉባኤው የሚመጡ እንግዶች የሚኖራቸው ቆይታ ምቹ እንዲሆን የሆቴልና አገልግሎት ዘርፍ ተቋማት ትልቁን ድርሻ ይይዛሉ።

ለዘንድሮ ጉባኤ የሚመጡ እንግዶች አየር ማረፊያ ከደረሱ በኋላ ወደ ሆቴሎች የሚያመሩ ሲሆን፤ ሆቴሎች በመልካም መስተንግዶና ኢትዮጵያን ይበልጥ በሚገልፅ መንገድ እንግዶችን መቀበል አለባቸው ሲሉ ገልጸዋል።

ከተለያዩ ሀገራት ተነስተው በመሪዎች ጉባኤ ላይ የሚካፈሉ እንግዶች ላይ ከመጠን ያለፈ የአገልግሎትና የሆቴል ክፍያ ማስከፈል እንደማይገባ አሳስበው፤ እንግዶችን የምንቀበልበት መንገድ የግል ጥቅምን ባስቀደመ መልኩ ሳይሆን የሀገርን ጥቅም ባስቀደመ መልኩ ሊሆን ይገባል ብለዋል።

ሆቴሎች ለጉባኤው አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረግ እንዳለባቸው ጠቁመው፤ ከደኅንነት አንፃር ከብሔራዊ መረጃና ደኅንነት ፤ከፌዴራል ፖሊስ፤ከአዲስ አበባ ፖሊስና ከኦሮሚያ ፖሊስ በጋራ በመሆን ጉባኤው እስከሚጠናቀቅ ድረስ አስፈላጊው ዝግጅት መደረጉን አስታውቀዋል።

ለጉባኤው ቅድመ ዝግጅት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተቋቋመውና ከ30 በላይ ተቋማትን ያካተተ ብሔራዊ ኮሚቴ ተዋቅሮ እየሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ሰላማዊት ዳዊት በበኩላቸው ፤ በባለፈው ዓመት በኮቪድ 19 ወረርሽኝና በሰሜኑ ግጭት ምክንያት የሆቴል ዘርፉ ትልቅ ፈተና ገጥሞት እንደነበር አስታውሰው፤ ዘንድሮ ግን ጉባኤውን ከኮቪድ ተፅዕኖ በተላቀቅንበትና ከሰላም ስምምነቱ በኋላ የምናስተናግደው በመሆኑ ለሆቴል ዘርፉ መነቃቃት ዕድል የሚፈጥር ነው ብለዋል።

የዘንድሮው የመሪዎች ጉባኤ ከቱሪዝም አኳያ የተለያዩ መነቃቃቶችን የሚፈጥር መሆኑን የገለፁት ወይዘሮ ሰላማዊት፤ በተለይ ከሆቴሎች ጋር ተያይዞ ለገቢያቸው ማደግ የሚረዱ ሁነቶች እንደሚፈጠሩ ጠቁመዋል።

ይሄንን ትልቅ ጉባኤ ስናዘጋጅ ከአስጎብኚ ድርጅቶች ጋር ሰፊ ሥራዎች መሠራታቸውን ጠቅሰው እንግዶችን ፍፁም ኢትዮጵያዊ በሆነ ሥርዓት ማስተናገድ ይኖርባቸዋል ብለዋል።

36ተኛው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤን መሠረት አድርጎ ከአየር ማረፊያ ጀምሮ እስከ መሰብሰቢያ አዳራሽ እንዲሁም ሆቴሎች ድረስ ሳቢና በጥሩ ሁኔታ የተዘጋጁ የማስታወቂያ ቪዲዮዎች በጎዳናዎች ላይ እንደሚሰቀሉ አስታውቀዋል።

በተጨማሪም ከባንኮች ጋራ በመተባበር እንግዶች ቀላል በሆነ መንገድ መስተናገድ እንዲችሉ የዘመናዊ የፋይናንስ ሥርዓት ካርድ (ስማርት ካርድ) የተዘጋጀ መሆኑን ገልጸዋል።

41ኛው የአስፈጻሚዎች ምክር ቤት ጉባኤ እና 36ኛው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ ከየካቲት 8 እስከ የካቲት 12 ቀን 2015 ዓ.ም በአዲስ አበባ ይካሄዳል።

ዜና

# በ3 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር የተገነባው የድሬዳዋ ወደብና ተርሚናል አገልግሎት መስጠት ጀመረ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በ3 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር ወጪ የተገነባው የድሬዳዋ ወደብና ተርሚናል ትናንት ተመርቆ አገልግሎት መስጠት ጀመረ።

የደረቅ ወደብ እና ተርሚናሉን የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አሕመድ ሽዴ፤ የድሬዳዋ ከተማ ከንቲባ አቶ ከድር ጁሐር፡ የኢትዮጵያ የባሕር፣ ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ አገልግሎት ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሮባ መገርሳ እና ሌሎች ከፍተኛ ባለስልጣናት መርቀው ከፍተውታል።

የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አሕመድ ሺዴ የድሬዳዋ ደረቅ ወደብና ተርሚናል የንግድ ሥርዓቱን እና ኢንቨስትመንት የመሳብ አቅምን ከፍ የሚያደርግ መሆኑን ተናግረዋል።

የድሬዳዋ ደረቅ ወደብና ተርሚናል በመንግሥት ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠውን የወጪና ገቢ ንግድ በማሳለጥ የተቀላጠፈ የሎጀስቲክስ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል መሆኑን ገልፀዋል።

የአገሪቱን የገቢ እና ወጪ ንግድ እንቅስቃሴዎች በከፍተኛ ደረጃ በማሳደግ ለሁለንተናዊ የምጣኔ ሃብት ዕድገትና የውጭ ምንዛሪ ከፍተኛ ሚና እንደሚኖረው አመላክተዋል።

የኢትዮጵያ የባሕር፣ ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ አገልግሎት ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሮባ መገርሳ፥ የድሬዳዋ ወደብ እና ተርሚናሉ በ34 ነጥብ 1 ሄክታር መሬት ላይ ያረፈ ሲሆን ባለሦስት ወለል የቢሮ ሕንፃ፣መጋዘን፣የኮንቴይነር ተርሚናልና 10 ሄክታር የውስጥ ለውስጥ የኮንክሪት መንገድ አለው ብለዋል።

ከሁለት ዓመታት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በከፍተኛ ወጪ የተገነባው ወደቡ በዓመት 128 ሺህ ኮንቴነር የማስተናገድ አቅም ያለው ሲሆን፤ ለድሬዳዋ ከተማ የኢኮኖሚ መነቃቃትን የሚፈጥርና ለበርካታ የከተማዋ ሥራ ፈላጊዎች የሥራ እድል የፈጠረ መሆኑ ተገልጿል።

በተጨማሪም በአንድ ጊዜ 140 መኪናዎች ማቆም የሚያስችል የተገነባ ቦታ፣ ሁለት የዕቃ ማስቀመጫ መጋዘን እንዲሁም ወደቡን ከኢትዮ ጅቡቲ ባቡር መስመር የሚያገናኝ የባቡር ሃዲድ የተሠራለት መሆኑ ታውቋል።

በቻይናው ሲ.ሲ.ኢ.ሲ.ሲ ተቋራጭ የተገነባው ወደቡ በ34 ነጥብ 1 ሔክታር ላይ ማረፉ ተገልጿል።

የድሬዳዋ ወደብ ከዚህ ቀደም ከኢትዮ ጅቡቲ በውሰት በወሰደው 0 ነጥብ 5 ሄክታር ላይ አገልግሎት ሲሰጥ መቆየቱን የወደቡ አስተዳደር አካላት ገልጸዋል።

የደረቅ ወደብ እና ተርሚናሉ የሀገሪቱን የገቢ እና ወጪ ንግድ እንቅስቃሴዎች በከፍተኛ ደረጃ በማሳደግ ለሁለንተናዊ የምጣኔ ሃብት ዕድገትና የውጭ ምንዛሪ ከፍተኛ ሚና እንደሚኖረው ተመላክቷል።

በምረቃ ሥነ ሥርዓቱ ላይ የኢትዮጵያ ባሕር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት አዲስ ብራንድ ይፋ ተደርጓል።

# «በአዲስ ሃሳብ ተስፋ ሰንቆ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ በቅርብ ጊዜያት ያጋጠሙ ችግሮች በሙሉ አቅምና ቆራጥነት ወደ መፍትሔው ሊገፋፉን ይገባል። የወረስናቸውን ስህተቶች ነቅሰን በመጣል በምትኩ መልካም ዘር ከዘራን፤ ልፋታችን መልካም ፍሬ ያፈራል፤ ለልጅ ልጆቻችንም የተስፋ ስንቅ ይሆናቸዋል።

ለውጡ የሚያስከትላቸው ስብራቶችም ሆኑ ትሩፋቶች የሚታወቁት በትውልድ ቅብብሎሽ ውስጥ ነው። ጉዳዩ ከግለሰቦች ሐሳብነት ተነስቶ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ዕቅድ ሆኖ ሲተገበር፣ ቀስ በቀስ እየተዋሐደ አሠራር፣ አኗኗር፣ ልማድና ባሕሪይ ይሆናልም ብለዋል።

በቅርቡ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የመልቀቂያ ፈተና የተገኘውን ውጤት በአብነት በማንሳትም፤ ከብዙ ጥናትና ሙግት በኋላ ኩረጃና ስርቆትን በከፍተኛ ሁኔታ ለመቀነስ የተተገበረው የተማከለ የፈተና ስልት ያስገኘው ውጤት ከፍተኛ ማኅበረሰባዊ መደናገጥን እንደፈጠረ አስታውሰዋል።

ከተፈታኞቹ ሃምሳ ከመቶና ከዚያ በላይ ጥያቄዎቹን መልሰው ለማለፍ የቻሉት ተማሪዎች ቁጥር እጅግ አናሳ ናቸው። አንድ ተማሪ እንኳን ማሳለፍ ያልቻሉ ትምህርት ቤቶች ሁኔታ ተፈጥሯልም ሲሉም ነው ያስታወሱት። የትምህርት ጥራት ላይ ያሉ ችግሮችና ቀውስ ፍንትው አድርጎ ማሳየቱንም ነው የተናገሩት።

የትምህርት ሥርዓቱ ስብራት የተፈተኑትን ተማሪዎች፣ መምህራን ከተመለመሉበት፣ ከሠለጠኑበት መንገድ፣ አጠቃላይ የትምህርት ሥርዓቱ ከተመራበት ፖሊሲና አቅጣጫ ጋር የተያያዘ፤ ባለፉት አሥርተ ዓመታት የመጣንበትን የተንሻፈፈ ጉዞ ውጤት ያሳየ ነው።

ችግሩ በአንድ ሌሊት እንዳልተፈጠረ ሁሉ መፍትሔውም በአንድ አዳር አይመጣም። የትምህርት ጥራት ችግርን ለማስተካከል ረጅም ጊዜና ከባድ ዋጋ ይጠይቃል። እንዲህ ያለው ስብራት በአንድ ዘርፍ ብቻ ያለ ችግር ነው ብሎ ማሰብም ስህተት ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ልክ በትምህርት ዘርፉ ላይ መዛነፎች እንዳሉ ሁሉ፤ በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚው፣ በማኅበራዊው፣ በፍትሕም ሆነ በጸጥታ ዘርፍ በተመሳሳይ ለረጅም ጊዜ የዘለቁ ስብራቶች መኖራቸውንም ነው የጠቆሙት።

ዘላቂነትንና አዋጪነትን ታሳቢ ያላደረጉ ብድሮች፣ ደካማ የፕሮጀክት አፈጻጸሞች ፣ ብክነትና ስርቆት ስር የሰደዱ ችግሮች መሆናቸውንም ነው ያመለከቱት።

የተቋማት መቀንጨር፣ እጅግ ከፋፋይ የፖለቲካ ትርክትና ጽንፍ የወጣ ብሔርተኝነት፣ በእምነት ተቋማትና በማኅበራዊ ተቋማት ውስጥ ያሉ ፈተናዎች በውጭ ግንኙነት የነበሩ ድክመቶች፣ በሞራልና ዕሴቶች ላይ የደረሱ ስብራቶች ለድርብርብ ችግሮች መነሻ ከመሆናቸው አስቀድሞ ልክ እንደ ትምህርት ሥርዓቱ ተጋፍጦ ማስተካከል እንደሚገባም ነው ያመለከቱት።

ከፋፋይ የሆነው ትርክትና ጽንፍ የረገጠው ብሔርተኝነት ወርሶን ነበር። ዛሬ አንጻራዊ ነጻነት ሲኖር የችግሩን ልክ አካል ነስቶ አየነው። የጸጥታና የፍትሕ ተቋሞች በአግባቡ ተቋም ሆነው ተገቢው አቅምና ቁመና ሳይኖራቸው መቆየታቸውንም አመልክተዋል።

በነጻነትና ዴሞክራሲያዊ ዐውድ ሲፈተኑ ግን ስብራታቸው ጎልቶ ፈጥጦ ወጣ። በምዝበራ ተቦጥቡጦ፣ በብድር ጫና ደቅቆ የነበረው ኢኮኖሚ በዕድገት አመላካች ቁጥሮች ተጀቡኖ ሲጨበጨብለት ነበር፤ የተበደራችሁትን ክፈሉ ሲባል፣ የሕዝብን ኑሮ ማሻሻል ሲሳነው፣ የሥራ ፈላጊዎችን የሥራ ፍላጎት በከፊል እንኳን ማሟላት ሲያቅተው የስብራቱ ልክ መጋለጡንም አመልክተዋል።

ችግሮቹ ሥር የሰደዱ ቢሆኑም፤ ልካቸው ጎልቶ የታየውና የወጣው ሥርዓቱ በአንፃራዊ ነጻነት ሲፈተሽ ነው። ውስጥ ለውስጥ ስሩ መሬት ሲቆነጥጥና ድር ሲያደራ ቆይቶ የሀገርን ሕልውና ሊገዘግዝ ጥርስ ሲያበቅል ነበር ነው ያሉት።

ከትምህርት ሥርዓቱ አንፃር ላለፉት ብዙ ዓመታት የሄድንበት መንገድና ውጤቱን ብንረዳም ችግሩን ለማሻሻል ብዙ ጊዜ የሚፈጅ ሥራ ይጠብቀናል። በኢኮኖሚውና በፖለቲካ ሥርዓቱም ተመሳሳይ ሥራ ይጠብቀናል። በዴሞክራሲና በነጻነት ጥያቄዎች ምክንያት ሲንገዳገዱ ያየናቸው ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ተቋሞቻችን አቅማቸው የት ድረስ እንደሆነ እያየን ነው።

የሥራ ፈጠራና የብድር አከፋፈል አቅማችንም የኢኮኖሚያዊ ሥርዓታችንን ደካማነት ቁልጭ አድርገው አሳይተውናል። ችግሩ ዛሬ እንዳልተፈጠረ በማሰብ ትውልዱ ለመፍትሔው በኃላፊነት መሥራት ይጠበቅበታል። የስብራቶቻችንን ልክና የችግሮቻችንን ጥልቀት ተረድተን የማሻሻያ ርምጃዎችንም ተግባራዊ በማድረግ ላይ እንገኛለን።

# የኛ ባልሆነ ጥፋት ሳልተገባ ቅጣት ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

አለመሆኑን ተናግረዋል።

አቶ ሃብታሙ፤ ታህሳስ 26 ቀን 2015 ዓ.ም ንግድ ፈቃድ ለማደስ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ ስድስት ንግድ ፍቃድ ለማደስ የሚያስፈልጉ እንደገንዘብ፣ ፎቶ እና ሌሎች ነገሮችን ይዘው መሄዳቸውን ገልጸዋል።

በወረዳው የንግድ ፍቃድ እድሳት የሚሰጡ ባለሙያዎች ሁሉንም ነገር ማሟላቴን እና ለእድሳት የምከፍለውን ገንዘብ አጭር የጽሑፍ መልዕክት መክፈያ ቁጥር ሲላክልኝ እንደምከፍል ነግረውኛል ብለዋል።

የክፍያ ገንዘቡን ለማወቅ የሚረዳው አጭር የጽሑፍ መልዕክቱ ከታኅሣሥ 26 ጀምሮ እስከ ታኅሣሥ 27 እንዲሁም ታኅሣሥ 28 ጠዋት ድረስ አልተላከልኝም ያሉት አቶ ሃብታሙ፤ የእድሳት ቀን ማብቂያ እየደረሰ በመሆኑ አጭር የጽሑፍ መልዕክት እንዳልተላከልኝ ለማሳወቅ ታኅሣሥ 28 ቀን ከሰዓት አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ ስድስት ንግድ ጽሕፈት ቤት ብሄድም አገልግሎት እየሰጡ አልነበረም ብለዋል።

ጥር 1 ቀን 2015 ዓ.ም አጭር የጽሑፍ መልዕክት እንዳልተላከ ለማሳወቅ ሲሄዱ ግን የመክፈያው ቀን እንዳበቃ እና ከ102 ብር ክፍያው በተጨማሪ 2 ሺህ 500 ብር ቅጣት እንዲከፍሉ እንደተነገራቸው ገልጸው፤ በዚህም እጅግ ማዘናቸውንና ንግድ ቢሮው ያልተገባ ቅጣት እንደጣለባቸው ተናግረዋል።

ንግድ ፈቃድ ለማደስ የሄዱት አቶ ወልደየስ ድማሙ (ስማቸው የተለወጠ) በበኩላቸው፤ የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ በፈጠረው ችግር ያልተገባ ቅጣት እንድከፍል ነግሮኛል ብለዋል።

የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ቅጣት የሚያስከፍለው ዜጎችን ለማስተማር ሳይሆን ገቢ ለመሰብሰብ ነው ያሉት አቶ ወልደየስ፤ ተገልጋይ ንግድ ፍቃድ ለማደስ የሚከፍለውን ገንዘብ መቀበል የንግድ ቢሮ ኃላፊነት ነው። ቢሮው አዲስ ሲስተም የዘረጋ ከሆነም ሲስተሙን እንከን የለሽ ማድረግ የራሱ የቢሮው ኃላፊነት እንጂ የተገልጋዩ አይደለም ሲሉ ገልጸዋል።

የክፍያ መጠኑን የሚያመላክተው አጭር የጽሑፍ መልዕክት እስካልተላከ ድረስ መክፈል በማልችልበት ሁኔታ ውስጥ ሆኜ ቅጣት እንድከፍል ማድረግ ተገቢ አይደለም ያሉት አቶ ወልደየስ፤ የንግድ ፍቃድ እድሳት ሂደት ለጀመሩ መፍትሔ ማዘጋጀት የኃላፊዎቹ ሥራ እንደሆነ እና ቅጣቱ ተገቢ እንዳልሆነ ለአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ንግድ ጽሕፈት ቤት አሳውቄያለሁ ብለዋል።

ጽሕፈት ቤቱ ጉዳዩ ወደሚመለከተው አካል ማሳወቁን እንደገለፀላቸው በመናገርም የጥር ወር ካለፈ ተጨማሪ ክፍያ ስለሚኖር ወደ ክፍለ ከተማ ሄደው መጠየቃቸውን አስረድተዋል።

ክፍለ ከተማውም ከበላይ አካላት በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት እየሠራ መሆኑንና ምንም ማድረግ አንችልም የሚል ምላሽ እንደተሰጣቸው ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የንግድ ፈቃድ እድሳት ላይ ችግር ያጋጠማቸው ነጋዴዎች ቅሬታ ዙሪያ ምላሽ ለማግኘት ወደ አዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ያደረገው የስልክና የአካል ተደጋጋሚ ሙከራዎች አልተሳኩም።

# ባለፉት ስድስት ወራት...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

በጥቃቱ ሊደርስ የነበረ የ15 ቢሊዮን ብር ከኪሳራም ማዳን መቻሉ ተገልጿል።

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር አቶ ሰሎሞን ሶካ በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ በግማሽ ዓመቱ 2 ሺህ 049 የሳይበር አደጋ ሙከራዎችን በአስተዳደሩ ማክሸፍ ተችሏል።

በተለያዩ ዘርፎች 2 ሺህ 145 የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች ተደርገዋል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በድረ-ገፅ ጥቃት ከተፈጸመው 395 ጥቃት 381ዱን ማክሸፍ እንደተቻለ ጠቁመዋል። በማልዌር ጥቃት ደግሞ 547 ጥቃቶች ተሞክረው 145ቱን ማክሸፍ እንደተቻለ አቶ ሰለሞን ጠቁመዋል።

በአንጻሩ መሠረተ ልማቶች ላይ ትኩረት ያደረጉ 869 ጥቃቶች መፈጸማቸውንና ፤አገልግሎት ሰጪ መሠረተ ልማቶችን ለማቋረጥ 57 ሙከራዎች መደረጋቸውን አስታውቀዋል።

በሀገሪቱ ባሉ ተቋማት ሰርጎ ለመግባት 197 ሙከራ የተደረገ ሲሆን ሁሉም ሙከራዎች ሙሉ በሙሉ ማክሸፍ ተችሏል ሲሉ አስረድተዋል።

በሌላ በኩል ቴክኖሎጂዎችን ተጠቅሞ ገንዘብ የመመዝበር፣ የተገልጋዮችን ዳታ በመስረቅ እና ስም የማጥፋት 80 ሙከራዎች መደረጋቸውንም አቶ ሰለሞን አንስተዋል።

እንደ አቶ ሰለሞን ገለጻ፣ ባንኮች እና የፋይናንስ ተቋማት፣ የፀጥታና ደህንነት ተቋማት፣ የሚዲያ ተቋማት፣ የሕክምና ተቋማት፣ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች እና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሳይበር ወንጀለኞች የጥቃት ዒላማ ነበሩ።

በአጠቃላይ በተከናወኑ የሳይበር ጥቃት የማክሸፍ ሥራዎች በሀገሪቱ ላይ ሊደርስ የነበረ የ 15 ቢሊዮን ብር ኪሳራ ማዳን እንደተቻለ አቶ ሰለሞን ገልጸዋል።

በግማሽ ዓመቱ 64 ተቋማት ላይ የሳይበር ጥቃት ተጋላጭነት ዳሰሳ ተደርጓል ያሉት አቶ ሰለሞን፤ 27 የመንግሥት እና 37 የግል ተቋማት ላይ የዳሰሳ ጥናት ተደርጎ 340 የሳይበር ደህንነት ክፍተቶች ተገኝተዋል ሲሉ አስታውቀዋል።

በግማሽ ዓመቱ የተደረጉ የሳይበር ጥቃቶች እና የከሸፉት ሙከራዎች በሀገር ላይ ሊያደርሱ የሚችሉት ኪሳራ ከፍተኛ እንደነበር ዋና ዳይሬክተሩ ተናግረው፤ የሳይበር ደኅንነት ጥቃቶች ተሳክተው ቢሆን ከፍተኛ የኢኮኖሚ ኪሳራ ያጋጥም ነበር ብለዋል።

በመደበኛ ክትትልና ቁጥጥር፣ በድንገተኛ ፍተሻ እና በደንበኞችና ተቋማት ጥያቄ መሠረት የሳይበር ጥቃት ሙከራዎችን ማክሸፍ እንደተቻለ ጠቁመዋል።

# የኢትዮጵያ ንግድ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ደንበኞች ቁጥርን ወደ ሰባት ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ማሳደግ መቻሉን እና 99 አዳዲስ የኢቲኤም ማሽኖችን መትከሉን የባንኩ ፕሬዚዳንት አቶ አቤ ሳኖ አክለው ተናግረዋል።

እንደ ባንኩ ፕሬዚዳንት ገለፃ፤ ከልዩ ልዩ የባንኩ የተቀማጭ ሂሳብ አገልግሎቶች 88 ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር ተቀማጭ ማሰባሰብ የተቻለ ሲሆን፤ የባንኩ አጠቃላይ ተቀማጭ ከነበረበት 890 ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር ወደ 978 ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር ደርሷል ብለዋል።

ባንኩ በውጪ ምንዛሪ ግኝት እና ሥርጭት ክንውኑ አንድ ነጥብ ሰባት ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር በመሰብሰብ የግማሽ ዓመቱን እቅድ 111 በመቶ ማሳካት ችሏል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ በዚህም ለገቢ ንግድ እና ለውጪ ምንዛሪ ለሚያስፈልጋቸው የንግድ እንቅስቃሴዎችም ሦስት ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ማቅረብ ችሏል ሲሉ አስረድተዋል።

በግሉ ዘርፍ እና በመንግሥት ለሚካሄዱ የልማት ፕሮጀክቶች በባንኩ ከቀረበው ብድር ውስጥ በግማሽ ዓመቱ 55 ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር የብድር ተመላሽ ተሰብስቧል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ለሚካሄዱ የግል እና የመንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች እና የንግድ እንቅስቃሴዎች ባጠቃላይ 66 ነጥብ ሶስት ቢሊዮን ብር ባንኩ አቅርቧል ብለዋል። በዚህም ባንኩ የሰጠው የብድር መጠን 975 ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር መድረሱን ገልጸዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የሞቃዲሾው መድረክ አገራቱ በቀጣናው ዘላቂ ሰላም ለማስፈን ያላቸውን ቁርጠኝነት ያሳየ ነው!

ቀጣናዊ ሰላምና መረጋጋት በአካባቢው የሚገኙ ሕዝቦችን ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ግንኙነት ለማሳደግ የሚኖረው ሚና የላቀ ፤ የቀጣናው ሕዝቦች በጋራ ወደሚፈልጉት ኢኮኖሚያዊ ብልጽግና ለመድረስ ለሚያደርጉት ጥረት ስኬትም ያለው አስተዋጽኦ ከፍ ያለ ነው። ነገን በተሻለ ተስፋ እንዲጠብቁም የሚኖረው አስተዋጽኦ መተኪያ የሌለው ነው።

በተለይም የብዙዎችን ዓይንና ቀልብ በሚስቡ አካባቢዎች (ቀጣናዎች) ያሉ አገራት ፤ ሊኖርባቸው ከሚችለው የውጭ ጣልቃ ገብነት አንጻር፤ የአካባቢያቸውን ሰላም በትብብር እውን ለማድረግ የሚሄዱበት መንገድ ለሕዝቦቻቸው ዘላቂ ሰላም ማጎናጸፍ የሚያስችል ነው። የልማት ስራዎችን በማስፋፋት የሕዝቦቻቸውን ኑሮ ለማሻሻል ለሚያደርጉት ጥረትም ወሳኝ አቅም ነው።

ሰላምና መረጋጋት በሰፈነባቸው ቀጣናዎች የሚገኙ አገራት ፤ አጋጣሚውን እንደ አንድ መልካም እድል በመጠቀም፤ በመካከላቸው ያለውን አቅም ለጋራ የሕዝቦች ተጠቃሚነት ማዋል ይችላሉ፤ ቀጣይ እጣ ፈንታቸውን በጋራ ወስነው የሕዝቦቻቸውን ነገዎች ብሩህ ለማድረግ የሚያስችሉ የጋራ የልማት ውጥኖችን አቅደው በቀላሉ መፈጸም ይችላሉ።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአፍሪካ ቀንድ (በምስራቅ አፍሪካ) የሚገኙ አገራት መሪዎች በአካባቢያቸው ዘላቂ ሰላም እና መረጋጋት በማስፈን በአገራቱ መካከል የነበረውን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ትስስር በማጠናከር ሕዝቦቻቸውን የግንኙነቱ የተሻለ ተጠቃሚ ለማድረግ በጋራ እያደረጉት ያለው ጥረትና እየተመዘገበ ያለው ውጤት ለዚሁ እውነታ እንደ አንድ ማሳያ ሊጠቀስ የሚችል ነው።

የአፍሪካ ቀንድ (የምስራቅ አፍሪካ) ቀጣና የብዙዎች ዓይን ያረፈበት ፤ ስትራቴጂክ ጠቀሜታውም ከፍያለ ነው። ከዚህ አንጻር የአካባቢውን አገራት መሪዎች በቀጠናው ዘላቂ ሰላምና መረጋጋት ለማስፈን እያደረጉት ያለው ጥረት በአካባቢው ሊኖር የሚችለውን የውጭ ጣልቃ ገብነት መቀነስ የሚያስችል እንደሆነ ይታመናል። ከዚህም ባለፈ በአካባቢው ዙሪያ በሚነሱ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን ዓለም አቀፍ ተደማጭነት ያሳድገዋል።

ይህ ደግሞ አሁን ባለንበት ዓለም አቀፍ የኃይል አሰላለፍና የአሰላለፍ ተጠቃሚነት የአካባቢው አገራት ሊኖራቸው የሚችለውን የመደራደር አቅም ከማሳደጉም በላይ፤ የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው ለመወሰን የጀመሩትን አዲስ የፖለቲካ መንገድ በማጠናከር የሕዝቦቻቸውን ተጠቃሚነት በተጨባጭ ማረጋገጥ የሚያስችል እድል ሊፈጥር የሚችል ነው።

ከዚህም ባለፈ ለቀጣናው የሰላም ጠንቅ የሆኑ አልሸባብን የመሳሰሉ ዓለም አቀፍ የሽብር ቡድኖች በአካባቢው መሰረት እንዳይኖራቸው ከማድረግ ጀምሮ፤ ሊፈጥሩት የሚችለውን የሰላም እጦትና ጥፋት ለማስቆም አገራቱ በጸጥታና ደህንነት ዙሪያ የሚያደርጉት ትብብር የሚበረታታና ከፍያለ እውቅና ሊሰጠው የሚገባ ነው።

ትብብሩ በቀጠናው ሰላምና መረጋጋት ከማስፈን ባለፈ ዓለም አቀፍ ኢንቨስትመንትን ወደ ቀጣናው በመሳብ የአካባቢው አገራት ሕዝቦችን የመልማት ፍላጎት እውን በማድረግ፤ በልማት ዙሪያ የነበረውን የቀደመ ትርክትና ከትርክቱ በስተጀርባ የነበረውን አንገት አስደፊ እውነታ መለወጥ የሚያስችል አቅም የሚገነባ ነው።

በተለይም ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ ወደ ሥልጣን ከመጡ ማግስት ጀምሮ ፤ የአካባቢውን ሕዝቦች ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ግንኙነት ወደላቀ ደረጃ ለማሳደግና በአገራቱ መካከል ያለውን ግንኙነት በመተማመን እና በመተባበር ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ያደረጉት/እያደረጉ ያለው ጥረት ለዚህ ተጠቃሽ ነው።

ይህ የቀጣናው አገራት ሕዝቦች ግንኙነታቸውን በማጠናከር ቀጣይ እጣ ፈንታቸው ላይ የጋራ ግንዛቤ ይዘው፤ በጋራ መንቀሳቀስ የሚያስችላቸው ታሪካዊ እውነታ ፤ በጸጥታው ዘርፍ ዓለም አቀፉን አሸባሪ ቡድን (አልሸባብን) በጋራ ከመዋጋት ጀምሮ የሶማሊያን ደህንነት ለማስጠበቅ በሚደረገው ርብርብ ጎልቶ እየታየ ይገኛል።

ለዚህም ከትናንት በስቲያ የቀጠናው አገራት መሪዎች (የኢትዮጵያ፣ ኬንያ ፣ ሶማሊያ እናጅቡቲ) በተገኙበት በዓለም አቀፍ አሸባሪው ቡድን/አልሸባብ ላይ የሚደረገውን ዘመቻ አጠናክሮ ለመቀጠል በሚቻልበት ሁኔታ ላይ በሞቃዲሾ የተካሄደው መድረክ አንድ ማሳያ ነው።

በወቅቱም የቀጠናው አገራት የሶማሊያን የጸጥታ ኃይሎች ለማሰልጠን ያሳዩት መነሳሳት የዚሁ እውነታ ሌላኛው መገለጫ ነው። ትብብሩ አሁናዊውን ቀጣናዊ ሰላም ከማስፈን ባለፈ፤ በቀጣይም በቀጣናው ሰላም ለማስፈን አገራቱ ያላቸውን ቁርጠኝነት በተጨባጭ የታየበት ነው!


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


## «የትናንት ስህተታችን የፈጠረውን የዛሬ ስብራታችንን ተረድተን ዘላቂ መፍትሔ ከሚፈጥሩት ወገን ለመሆን መዘጋጀት አለብን»

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ

**ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ትናንት በማሕበራዊ ትስስር ገጽ ያሰፈሩት መልእክት ሙሉ ቃል**

**«የትናንት ዘር፣ የዛሬ ፍሬ፣ የነገ ስንቅ!»**

አንድ ነገር የሚፈጠርበትና የሚታወቅበት ወቅት ሊለያይ ይችላል። ጽንስ ከተፈጠረ ከወራት በኋላ እርግዝና ሆኖ ይታያል፤ ሕጻን ሆኖ ለመወለድ ደግሞ ተጨማሪ ጊዜያትን ይወስዳል። የተወለደ ሕጻን አድጎና ጎልብቶ፣ ስብዕናውና ባህርይው ሙሉ ለሙሉ የሚታወቀው ደግሞ ከዓመታት በኋላ ነው። የሕይወት ትልቁ ምስጢር፣ ትናንት በማይታየው ጽንስና በጨቅላው ሕጻን ውስጥ የዛሬው ትልቅ ሰው ተሰውሮ መኖሩና ማደጉ ነው። የነገውን ማንነትና ውጤት ዛሬ የሚደረጉ እርምጃዎችና ማስተካከያዎች ሊቀርጹትና ሊያርሙት መቻላቸው ደግሞ ተስፋ የሚሰጥ እውነታ ነው።

የሰብልም ሆነ የአረም ዘር በእርሻ መሬት ውስጥ የሚኖርበትና፣ በቅሎና አድጎ የሚገለጥበት ጊዜ የተለያየ ነው። ዛፉ በዘሩ ውስጥ ይኖራል፤ እንደሚያገኘው አፈር፣ አየር፣ ብርሃንና እንክብካቤ በጊዜ ሂደት ውስጥ ሙሉ ማንነቱ ይገለጣል። ልክ እንደ ሥነ ሕይወታዊ ዘር ሁሉ፣ በማኅበረሰብ ውስጥ የሚዘራ የሃሳብ ዘርም አድጎና ጎልብቶ፣ አብቦና አፍርቶ በሰዎች ዙሪያ ተጨባጭ ሆኖ ለመገለጥ ዘለግ ያለ ጊዜ ይፈጃል። ለዚያም ነው ያልተገለጠን ነገር እንደሌለ አድርጎ የመውሰድ፣ አልፎ ተርፎም ነገሩ በተገለጠበት ጊዜ እንደ ተፈጠረ አድርጎ የመገንዘብ ዝንባሌ ስህተት የሚሆነው።

በተለይ ሥርዓታዊ ለውጥ፣ በጎም ሆነ ክፉ ውጤቱ በአጭር ጊዜ አይታይም፤ አይመዘንም። ለለውጡ መነሻ የሆኑ ሃሳቦች በግለሰቦች ውስጥ ሠርጾ፤ ልማድና ሥርዓት ሆኖ፤ የማኅበረሰቡ ማንነት መገለጫ ባህል እስከሚሆን ድረስ ዘመናት ይፈጃል። ለውጡ የሚያስከትላቸው ስብራቶችም ሆኑ ትሩፋቶች የሚታወቁት በትውልድ ቅብብሎሽ ውስጥ ነው። ጉዳዩ ከግለሰቦች ሃሳብነት ተነስቶ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ዕቅድ ሆኖ ሲተገበር፣ ቀስ በቀስ እየተዋሃደ አሠራር፣ አኗኗር፣ ልማድና ባህሪይ ይሆናል። እንደ ወረርሽኝ በጥቂቶች ጀምሮ ብዙኃንን ይወርሳል። ከአንድ አካባቢ ተነስቶ አገርን ያዳርሳል። ይሄንን የለውጥ ሂደት መረዳት ላልቻሉ፤ ጅማሬውንና ዕድገቱን በትክክል ለማያስተውሉ የሚፈጠሩ ለውጦች ሁሉ ድንገቴና ማኅበረሰባዊ ድንጋጤን የሚያስከትሉ ናቸው።

በቅርቡ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የመልቀቂያ ፈተና የተገኘው ውጤት ለዚህ ጥሩ ማሳያ ነው። ከብዙ ጥናትና ሙግት በኋላ ኩረጃና ሥርቆትን በከፍተኛ ሁኔታ ለመቀነስ ተግባራዊ የተደረገው የተማከለ የፈተና ስልት ያስገኘው ውጤት ከፍተኛ ማኅበረሰባዊ መደናገጥን ሲፈጥር ታይቷል። ከተፈታኞቹ ሃምሳ ከመቶና ከዚያ በላይ ጥያቄዎቹን መልሰው ለማለፍ የቻሉት ተማሪዎች ቁጥር እጅግ አናሳ ናቸው። በሺህ የሚቆጠሩ ትምህርት ቤቶች አንድ ተማሪ እንኳን ለማሳለፍ ያልቻሉበት ሁኔታ ተፈጠረ። ይህም የትምህርት ጥራት ላይ ያሉብንን ችግሮችና ያለንበትን ቀውስ ፍንትው አድርጎ አሳየን።

የችግሩን ልክ በአግባቡ፣ በአሐዝ መረጃ የተገነዘብነው እና ያየነው አሁን ቢሆንም፣ ችግሩ ግን በፈተናው የተገለጠ እንጂ የተፈጠረ አይደለም። የትምህርት ሥርዓቱ ስብራት ዛሬ የተፈተኑትን ተማሪዎች የሚያስተምሩ አስተማሪዎች ከተመለመሉበት፣ ከሠለጠኑበት መንገድ፣ አጠቃላይ የትምህርት ሥርዓቱ ከተመራበት ፖሊሲና አቅጣጫ እና ከሌሎች ብዙ ጉዳዮች ጋር ተያይዞ፤ ባለፉት አሥርት ዓመታት የሄድንበት የተንሻፈፈ ጉዞ ውጤት ነው። ዛሬ የችግር ሰብሉን ብናጭድም ዘሩ አፈር ነክቶ መብቀል ከጀመረ ዘመናት ተቆጥረዋል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ አንድ እውነት ማወቅ አለብን፤ ችግሩ በአንድ ሌሊት እንዳልተፈጠረ ሁሉ መፍትሔውም በአንድ አዳር ሊመጣ አይችልም። ዛሬ ከአበባ አልፎ ፍሬውን ያየነውን የትምህርት ችግር ቀልብሶ ለማስተካከል ረጅም ጊዜና ከባድ ዋጋ ይጠይቃል። እንዲህ ያለው ስብራት በአንድ ዘርፍ ብቻ ያለ ችግር ነው ብሎ ማሰብ ስህተት ነው።

ልክ በትምህርት ዘርፉ ላይ መዛነፎች እንዳሉብን ሁሉ፤ በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚው፣ በማኅበራዊው፣ በፍትሕም ሆነ በጸጥታ ዘርፍ በተመሳሳይ ለረጅም ጊዜ የዘለቁ ስብራቶች አሉብን። ዘላቂነትንና አዋጪነትን ታሳቢ ያላደረጉ ብድሮች፣ ደካማ የፕሮጀክት አፈጻጸሞች፣ ብክነትና ሥርቆት፣ የተቋማት መቀንጨር፣ እጅግ ከፋፋይ የፖለቲካ ትርክትና ጽንፍ የወጣ ብሔርተኝነት፣ በእምነት ተቋማትና በማኅበራዊ ተቋማት ውስጥ ያሉ ፈተናዎች፣ በውጭ ግንኙነት የነበሩ ድክመቶች፣ በሞራልና እሴቶች ላይ የደረሱ ስብራቶች፣ ወዘተ. ባለፉት ብዙ አሥርት ዓመታት በሂደት ተፈጥረውና ተንሰራፍተው ቆይተዋል። እነዚህን ስብራቶች ልክ እንደ ትምህርት ሥርዓቱ የሚጋፈጣቸው ካላገኙ ሳይገለጡ የመኖርና ለድርብርብ ችግሮች መነሻ የመሆን እድላቸው ሰፊ ነው።

አንድ ገበሬ ዘሩን ከመዝራቱ በፊት በእርሻ ወቅት ነቅሎና ጎልጉሎ ያልጣላቸው የአረም ሰርዶዎች ሥራቸውን ከመሬት በታች ቀብረው የሌሉ ቢመስሉም፤ ዋናውን ችግር የሚፈጥሩት የኋላ ኋላ ለመልካም ዘሩ የሚፈሰውን ውሃና ማዳበሪያ ተሻምተው ካደጉ በኋላ ነው። በዚህም የተነሳ ያ ገበሬ ቀድሞ መንቀልና መጎልጎል በተገባው ጊዜ ከሚያፈሰው ጉልበት በላይ ዋጋ ከፍሎ በአረም ወቅት ለዳግም ልፋት ይዳረጋል። ለዚያም ነው ማኅበረሰባችን ለረጅም ዘመን ካዳበረው እውቀት ተነስቶ “አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ” የሚለው። ትናንት እንደ አገር ነቅሰን ያልጣልናቸው ፖለቲካዊና ማኅበራዊ አረሞች የሌሉ እስኪመስሉ ድረስ ሥራቸውን ደብቀው በመቆየታቸው፣ አሁን ምቹ አጋጣሚዎችን እየጠበቁ ለመልካም ልምምዶች የሚፈስላቸውን ፖለቲካዊ ወረቶች ሲሻሙ እያስተዋልን ነው።

ባለፉት ብዙ አሥርት ዓመታት በአፈናና በጉልበት ችግሩን ሸፋፍነነው የሌለ ቢመስለንም፣ ከፋፋይ የሆነው ትርክትና ጽንፍ የረገጠው ብሔርተኝነት ወርሶን ነበር። ዛሬ አንጻራዊ ነጻነት ሲኖር የችግሩን ልክ አካል ነሥቶ አየነው። የጸጥታና የፍትሕ ተቋሞቻችን በአግባቡ ተቋም ሆነው ተገቢው አቅምና ቁመና ሳይኖራቸው፣ በማስፈራራትና በአምባገነናዊ ዐውድ ልክ እንደ ፅጉራም ውሻ ከባድ ጡንቻ ያላቸው መስለው ይኖሩ ነበር። በነጻነትና ዴሞክራሲያዊ ዐውድ ሲፈተኑ ግን ስብራታቸው ጎልቶ ፈጥጦ ወጣ። በምዝበራ ተቦጥቡጦ፣ በብድር ጫና ደቅቆ የነበረው ኢኮኖሚ በዕድገት አመላካች ቁጥሮች ተጀቡኖ ሲጨበጨብለት ነበር፤ የተበደራችሁትን ክፈሉ ሲባል፣ የሕዝብን ኑሮ ማሻሻል ሲሳነው፣ የሥራ ፈላጊዎችን የሥራ ፍላጎት በከፊል እንኳን ማሟላት ሲያቅተው የስብራቱ ልክ ተጋለጠ።

ችግሮቹ ሥር የሰደዱ ቢሆኑም፤ ልካቸው ጎልቶ የታየውና የወጣው ሥርዓቱ በአንፃራዊ ነጻነት ሲፈተሽ ነው። ነጻነት በሌለበት፣ ሁሉም ታፍኖና ተዘግቶ በፍርሃት በተሸበበበት፣ ጭራሽ ችግሮቹ ጌጥ መስለው ሊታዩ ይችላሉ። እውነቱ ግን ውስጥ ለውስጥ ሥሩ መሬት ሲቆነጥጥና ድር ሲያደራ ቆይቶ የአገርን ህልውና ሊገዘግዝ ጥርስ ሲያበቅል ነበር።

አሁን ከትምህርት ሥርዓቱ አንፃር ላለፉት ብዙ ዓመታት የሄድንበት መንገድና ውጤቱን መረዳት ብንችልም፣ ችግሩን ለማሻሻል ግን ገና ብዙ ጊዜ የሚፈጅ ሥራ ይጠብቀናል። ችግሩን አውቀነዋል ማለት ዛሬውኑ ፈትተን እንጨርሰዋለን ማለት አይደለም። በኢኮኖሚውና በፖለቲካ ሥርዓታችን ተመሳሳይ ሥራ ይጠብቀናል። በዴሞክራሲና በነጻነት ጥያቄዎች ምክንያት ሲንገዳገዱ ያየናቸው ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ተቋሞቻችን አቅማቸው የት ድረስ እንደሆነ እያየን ነው።

የሥራ ፈጠራና የብድር አከፋፈል አቅማችንም የኢኮኖሚያዊ ሥርዓታችንን ደካማነት ቁልጭ አድርገው አሳይተውናል። የችግሩን ልክ ዛሬ ብንረዳም፣ ችግሩ ዛሬ እንዳልተፈጠረ እያሰብንና የመፍትሔ ምንጮች እኛ የዛሬዎቹ ትውልዶች መሆናችንን እያመንን በኃላፊነት እንሥራለን። የስብራቶቻችንን ልክና የችግሮቻችንን ጥልቀት በሚገባ ተረድተን የማሻሻያ እርምጃዎችንም ተግባራዊ በማድረግ ላይ እንገኛለን።

ለረዥም ዘመን ሳይገለጥ፣ አልፎ ተርፎም እንደ ትክክለኛ ነገር ሲቆጠር የኖረን ማኅበራዊ ስብራት በሆነ አጋጣሚ ተገልጦ ፊት ለፊት ሲጋፈጡት በመጀመሪያ በድንጋጤ ተውጦ የሚያደርጉት ቢጠፋ እምብዛም አይደንቅም፤ ተፈጥሯዊ ምላሽም ነው።

ነገር ግን ጉዳዩንና የነገሩን መሠረት ለመካድ መሞከር ወይም ሰንካላ ሰበብ እያስቀመጡ ማለፍ ለችግሮች ዘላቂ መፍትሔ አያመጣም። ለወባ በሽታ የወባ መድኃኒት እንጂ፣ ገና ለገና በሽታው እንደ ራስ ምታትና ብርድ ብርድ የማለት ምልክቶችን አሳየ ተብሎ የብርድና የራስ ምታት ማስታገሻ መድኃኒቶችን እንደ ዘላቂ መፍትሔ አይወሰድም። ችግሮች ሲገጥሙ ጣት መጠቆምና በቀዳዳ ሾልኮ ማምለጥ የሞኞችና የፈሪዎች መፍትሔ ሲሆን፤ ትክክለኛው የብልህና የጀግኖች መንገድ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ፊት ለፊት ተጋፍጦ በጥበብ ለመርታት መፍጨርጨር ነው።

የትናንት ስህተታችን የፈጠረውን የዛሬ ስብራታችንን ተረድተን ዘላቂ መፍትሔ ከሚፈጥሩት ወገን ለመሆን መዘጋጀት አለብን። በቅርብ ጊዜያት የሚያጋጥሙን ችግሮች ጥልቀታቸው በሙሉ አቅምና ቆራጥነት ወደ መፍትሔው እንድንገባ ሊገፉፉን ይገባል። በአዲስ ሃሳብና ጉልበት ለመገስገስ ተስፋ ሰንቀን እንነሳ፤ ለላቀ ለውጥና ለተሻለ ነገ እንትጋ። እንደ አገርና እንደ ማኅበረሰብ የሚያዋጣን መንገድ ይሄ ነው። ከትናንት የወረስናቸውን ስህተቶች ነቅሰን ከጣልንና በምትኩ ዛሬ መልካም ዘር ከዘራን፤ ያለ ጥርጥር ልፋታችን መልካም ፍሬ ያፈራል፤ ለልጅ ልጆቻችንም የተስፋ ስንቅ ይሆናቸዋል።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!**

**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

**ጥር 25፣ 2015 ዓ.ም**

# ነፃ ሃሳብ

# የሰላም መገኛ ሰላማዊ ተግባቦት ብቻ ነው

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵያ)**

የሰላም መገኛዋ መንገድ ሰላማዊ ተግባቦት ብቻ ነው። ከሰላማዊ ተግባቦት ውጪ ሰላም ሊያመጣ የሚችል ሃይል በምድር ላይ የለም። ሰላማዊ ተግባቦት አገርና ሕዝብን አስቀድሞ ፖለቲካዊ መሻትን ያስከተለ ነው። ሰላማዊ ተግባቦት ሁሉም ሰው የተለየ እና ልዩ ልዩ ሃሳብና ፍላጎት እንዳለው በመረዳት ያን ብዙ አይነት ሃሳብ ወደ ጠቃሚ አንድ ሃሳብ መቀየር ነው።

ሰላማዊ ተግባቦት የራስን ፍላጎት ወደ ጎን ብሎ የብዙሃኑን ፍላጎት ማስቀደም ነው። ይሄ ሁሉ ባልሆነበት ሁኔታ ላይ ሰላም ሊመጣ አይችልም። የሰላም መገኛዎችን ዘግቶ ሰላም ለማምጣት መሞከር መገለጫችን ሆኖ ለዘመናት ዘልቀናል። ሰላም ሊሰጡንና ሊያግባቡን የሚችሉ ብዙ የጋራ ትውፊቶቻችንን ችላ ብለን በሚለያዩን ጥቂት ነገሮች ላይ ጊዜ ስናጠፋ ከርመናል።

ይሄ ሁሉ አካሄድ የምንፈልጋትን አገር አልፈጠረልንም። አሁን አቅጣጫችንን መቀየር አለብን .. ባልሄድንባቸው መንገዶች መሄድ፣ ባልተመለከትነው አቅጣጫ መመልከት ይኖርብናል። ብዙዎች የሰላምን መገኛ መንገድ ሳያውቁ ሰላም ለማምጣት ብዙ ለፍተዋል። ሰላም አንድ ቦታ ነው ያለው እርሱን በመነጋገር ውስጥ ነው። መነጋገር ስንል መግባባት ያለበትን መነጋገር ነው።

ዓለም ሁሌም በመነጋገር ውስጥ ናት ፤ሁሉም መነጋገሮች ግን ሰላም ሲያመጡላት አይታይም። ይሄ የሆነው ደግሞ በራስ ወዳድነትና የአንድ ወገንን የበላይነት በማሳየት ነው። የአንድ ወገን የበላይነት በሚንጸባረቅነት ሁኔታ ላይ ሰላም የለም። ሰላም የእኩል ሃሳብ፣ የእኩል ተግባር ነጸብራቅ ነው።

አገራችን ለምን ሰላም ራቃት ብለን ስንጠይቅ ይሄን እውነት ነው የምናገኘው። እኛ አገር ሁሉም ነገር በእኩልነት ላይ ሲንጸባረቅ አይታይም። ፖለቲካችንን ብናየው የእኔነትና የራስ ወዳድነት እድፍ ያቆሸሸው ነው። የአንድ ቡድን የበላይነት የሚንጸባረቅበት ነው። ይሄ ግለኝነት ደግሞ መጨረሻው ጦርነት ነው። እንደ አገር ዘላቂ ሰላም ለመገንባት እኩል ሃሳብና እኩል ተግባር ያሻናል።

ከኖርንበት የጦርነት ልማድ ወጥተን መነጋገርን መሰረት ያደረገ አዲስ አብዮት ያስፈልገናል። ከነበርንበት የቂመኝነት አካሂድ ወጥተን እርቅን ያስቀደመ አዲስ አስተሳሰብ መላበስ ያስፈልገናል። አገራችን አሁን የሰላም አብዮት ነው የሚያስፈልጋት። የአንድነት፣ የመቻቻል አብዮት ነው የሚያስፈልጋት። ይሄን አዲስና ለዘመኑ የሚመጥን አካሄድ ነው መለማመድ ያለብን።

ለመነጋገር ከተሰናዳን ከጦርነት የሚሻሉ ብዙ ነገሮች አሉን። አገራችን በብዙ ነገር ላይ ኋላ ቀር ናት። ጦርነትና አለመግባባት ሲጨመርበት ነገሩ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ይሆናል። በየትኛውም መስፈርት እንየው ለአገራችን ጦርነት ሳይሆን ሰላም ነው የሚያስፈልጋት። ለሕዝባችን መለያየት ሳይሆን አንድነት ነው የሚያስፈልገው።

የተጀመረው ሰላም እንዲቀጥል፣ ቀጥሎም አስተማማኝ እንዲሆን ከትናንቱ የተለየ አዲስ ማንነት ያስፈልገናል። በዚህ አዲስ አስተሳሰብ፣ አዲስ ፖለቲካ፣ አዲስ ርዕዮተ ዓለም ካልሆነ አዲስና ሰላማዊ አገር መፍጠር አይቻለንም።

እውነተኛ ሰላም ተነጋግሮ በመግባባት ውስጥ ነው የሚገኘው። ሰው ተነጋግሮ መግባባት ካልቻለ አገር ሊለውጥ የሚችል እውቀትም ሞራልም እንደሌለው ነው የማምነው። ጥበብ ማለት.. እውቀት ማለት በብዙሃነት ውስጥ አንድ አገርና አንድ ሕዝብ መፍጠር ነው። ምርጥ ፖለቲከኛ ምርጥ ተናጋሪ ሳይሆን ምርጥ አሳቢ ነው።

ምርጥ ሃሳቦቻችን ናቸው ምርጥ ሀገር የሚፈጥሩልን። ምርጥ ሃሳቦቻችን ናቸው በብዙ ተቃርኖ፣ በብዙ የፖለቲካ ልዩነት ውስጥ ለአገር የሚበጅ እውነት የሚሰጡን። ምርጥ ሃሳቦቻችን ናቸው ከኋላቀርነትና ከዝግምና የሚያወጡን። ተነጋግሮ መግባባት ያልቻልነው ለአገር የሚበጅ፣ አገርን ያስቀደመ፣ ከእኔነት የወጣ ምርጥ ሃሳብ ስለሌለን ነው።

ምርጥ ሃሳብ ሁልጊዜም ማረፊያው አገርና ሕዝብ ነው። በቀሪ ጊዜአችን በምርጥ ሃሳብ ምርጥ አገር መፍጠር አለብን። በምርጥ ሃሳብ ምርጥ አገር ካልፈጠርን በብላሽ ሃሳብ ብላሽ ሀገር ፈጥረን ተበላሽተን ነው የምንቀረው። ይሄ ደግሞ ለማናችንም አይበጅም.. በእርቅና በተግባቦት ወደ ሰላም መሄዱ ነው። ለሁላችንም እኩል ዋጋ ያለው።

አገራችን ሃሳብ አላጣችም.. እንደ ሕዝብ ቁጥሯ፣ እንደ ወጣቷ ብዛት ለአገር የሚሆን ብዙ ሃሳብ አለን። ችግር የሆነብን የሃሳብ ልዩነቶቻችንን ወደአንድነት ማምጣቱ ላይ ነው። ችግር የሆነብን ልዩ ልዩ ሃሳቦቻችንን እንዴት በሰላማዊ መንገድ ለሰላማዊ ነገር መጠቀም እንዳለብን አለማወቃችን ነው።

> **አገራችን ሃሳብ አላጣችም.. እንደ ሕዝብ ቁጥሯ፣ እንደ ወጣቷ ብዛት ለአገር የሚሆን ብዙ ሃሳብ አለን። ችግር የሆነብን የሃሳብ ልዩነቶቻችንን ወደአንድነት ማምጣቱ ላይ ነው። ችግር የሆነብን ልዩ ልዩ ሃሳቦቻችንን እንዴት በሰላማዊ መንገድ ለሰላማዊ ነገር መጠቀም እንዳለብን አለማወቃችን ነው።**

በአግባቡ መጠቀም ከቻልን የተለያዩ ሃሳቦች በአንድ አገር ላይ ልማትም፣ ብልጽግናም ናቸው። በአግባቡ መጠቀም ካልቻልን ደግሞ ነውጥና ጦርነትን ነው የሚያስከትሉብን። አሁን የሚጠቅመን የሃሳብ ብዙሃነታችንን በሰላማዊ መንገድ ለልማት መጠቀም ነው። ያለፉ የጦርነት ታሪኮቻችን የሃሳብ ብዙሃነትን እንዴት መጠቀም እንዳለብን ካለማወቅ የመጣ ነው።

አንድ ሰው አንድ ሃሳብ ሲኖረው፣ አንድ ፖለቲከኛ ከሌላው ፖለቲከኛ አዲስ ሃሳብ ሲኖረው በራሳቸው መንገድ ሁሉም ለኢትዮጵያ አስተዋጽኦ እያደረጉ እንደሆነ ማወቅ አለብን። የትኛውም የሃሳብ ልዩነት ወደ ጦርነት ከማምራቱ በፊት ጠቃሚ ነው።

የሃሳብ ልዩነቶቻችን ኢትዮጵያን እንዲጠቅሙ እንጂ እንዲጎዱ መፍቀድ የለብንም። የፖለቲካ ልዩነታችን አገር እንዲቀይሩ ሕዝብ እንዲያሻግሩ እንጂ ለጦርነትና ለጉስቁልና እንዲዳርጉን መፍቀድ የለብንም። ይሄ ብላሽ አካሄድ ነው የሃሳብ ልዩነትን በአግባቡ እንዳንጠቀም እክል እየፈጠረብን ያለው።

አገርና ሕዝብን ያስቀደመ ፖለቲካና ፖለቲከኛ በሃሳብ ልዩነት አገር ይሰራል እንጂ ጦርነት አይፈጥርም። ከእኛ በፊት ኢትዮጵያ መቅደም አለባት። ከእኛ በፊት ሕዝብ መቅደም አለበት። ከሥልጣናችን በፊት፣ ከግል ጉዳያችን በፊት ትውልድ ይቅደም። ከአገር በፊት የግል ጉዳያችንን ማስቀደማችን ነው ዛሬ ላይ ለጦርነት እየዳረገን ያለው። ኢትዮጵያን እስካላስቀደምን ድረስ የምንፈልገውን ሰላም ማምጣት አንችልም። ኢትዮጵያን እስካላስቀደምን ድረስ አሁንም ቢሆን ተነጋግሮ ሰላም ማምጣት ይቸግረናል።

ሀገር በአንድ አይነት ሃሳብ አትገነባም። ለሀገር ግንባታ አሁን ላይ እዚም እዛም የምንሰማም ልዩ ልዩ ሃሳብ ያስፈልገናል። ልዩ ልዩ ሃሳቦቻችን ብልሃትን፣ ስኬትን፣ ተስፋን፣ እውቀትን፣ ልምድን ያነገቡ ናቸው። በሰላማዊ መንገድ በጠረጴዛ ዙሪያ ዘርግተን እንወያይባቸው እንጂ የአንተ ሃሳብ ከእኔ ሃሳብ አይገጥምምና ስንል ወደመለያየት መግባት አይኖርብንም።

ኢትዮጵያ መልከ ብዙ ናት። የተለያዩ መልኮች፣ የተለያዩ ባህሎች፣ የተለያዩ ወግና ሥርዓቶች ያቆነጇች ናት። ይቺ አገር እንዴት ሆና በአንድ አይነት ሃሳብ ብቻ ትቀጥላለች? ኢትዮጵያ ብዙ ናት.. ብዙ ሃሳብ፣ ብዙ እይታ ያስፈልጋታል። የሃሳብ ልዩነቶቻችን ወደጦርነት እንዳይወስዱን ተነጋግሮ መግባባትን መልመድ አለብን።

ተቻችሎ በጋራ መቆምን ባህል ማድረግ አለብን። የመጣው ሰላም በሁላችንም ልብ ላይ ተስፋን ለኩሷል። ሳቅ አድርጎልናል። እንደሳቅን እንድንቀጥል ሰላማችን እክል ሳይገጥመው መዝለቅ አለበት። ይሄ እንዲሆን ደግሞ ሰላም በሚያመጡ ነገሮች ላይ ብቻ እናተኩር።

ጦርነት በቃን.. ይሄ የሁሉም ኢትዮጵያውያን የጋራ ድምጽ ነው። በወንድማማች መካከል ፍቅር እንጂ መለያየት ዋጋ የለውም። ሲገሉንና ስንገልባቸው የነበሩ ሾተሎቻችን ወደ ሰገባቸው ይመለሱ። ሲያደሙንና ሲያጎሳቁሉን የነበሩ ጎራዴዎቻችን ወደ አፎታቸው ይመለሱ።

ፍቅር ነው የሚያስፈልገን.. ወንድማማችነት ነው የቀረን። ብዙ ነገሮችን ሞክረናል.. አሁን የሚቀረን ሰላምና እርቅ ነው። አሁን የሚቀረን ተነጋግሮ መግባባት፣ ተግባብቶ ሰላማዊ አገር መፍጠር ነው። ጦርነት የፈጠሩ ሃሳቦቻችንን ሰላም እንዲፈጥሩ እድል እንስጣቸው። መለያየትን የፈጠሩ ሃሳቦቻችንን አንድነትና ወንድማማችነትን እንዲያጸኑ እናስገድዳቸው።

ኢትዮጵያ ቀፏችን ናት.. ማር እንድትይዝ አርቀን የሰቀልናት ቀፏችን። ማር አበባ በሌለበት.. ምንድነው? ማር ንብ በሌለበት ምንድ ነው? አገራችን ማር እንድትይዝ ማር ሊሰጧት የሚችሉ ነገሮች ያስፈልጓታል። ከዚህ ውስጥ አንዱና ዋነኛው ሰላም ነው። አበባ በሌለበት ማር እንደሌለ ሁሉ ሰላም በሌለበትም አገር ምንም ናት።

አገራችን ማር እንድትይዝ፣ ህዝባችን ከማሩ እንዲበላ ማር የሚሰራ ሰላም ያስፈልገናል። ይሄ ባልሆነበት ሁኔታ ላይ ድካማችን ከንቱ ድካም ነው የሚሆነው። አንድን ነገር ስንፈልግ ያ ነገር የሚያስፈልገውን ግብዓት አሟልተን ነው መሆን ያለበት። አሁን ላይ አገራችን ከሰላም ውጪ ምንም አያስፈልጋትም።

የአገራችን ሰላም ደግሞ ከሰማይ የሚወርድ ሳይሆን በእኛ በልጆቿ የሚፈጠር ነው። በመግባባት፣ በውይይት የሚመጣ ነው። ፖለቲካውን በማስተካከል፣ የሃሳብ ልዩነቶችን ወደተግባቦት በመቀየር የሚመጣ ነው።

ዓለም እንደ ሰላም የክብር አክሊል የላትም። ሁሌም ጸጋዎች፣ ሁሉም ክብሮች ከሰላም ቀጥለው የሚመጡ ናቸው። ብዙ ነገር እያለን ምንም እንደሌለው የሆነው ከሁሉም ትልቁ ሰላም ስለጎደለን ነው። በሰላም ካልሆነ በምንም አንሞላም፣ በምንም አንትረፈረፍም። በሰላም መንገድ ከተጓዝን ብቻ ነው የኢትዮጵያን ችግሮች መፍታት የምንችለው። በምክክር መኖር ስንችል ብቻ ነው ለኢትዮጵያ የምንበጀው።

እንደ አገር በሰላማዊ ሃሳብ የቆመች ሰላማዊ አገር ታስፈልገናለች። ድልድይ እንሁን.. ማንም ወጥቶ የሚገባበት ድልድይ። በሰላም ሃሳብ የተገነባ ድልድይ። ከዚህ ወደ እዛ መሻገሪያ ድልድይ ያስፈልገናል። የጥል ግድግዳዎችን አፍርሰን፣ የመለያየት ግንቦችን ደርምሰን አዲስ ምስራቅ ማየት አለብን።

አዲስ ጸሀይ፣ አዲስ ጀምበር መሞቅ አለብን። ወደ ጦርነት የሚወስዱ መንገዶችን እየዘጋን የእርቅና የምክክር መንገዶችን መክፈት አለብን። የመለያየት መንገዶችን እየዘጋን የአንድነትና የወንድማማች መንገዶችን መስራት አለብን። ተስፈኛዋ ኢትዮጵያ በዚህ እውነት ውስጥ ብቻ ነው የምትፈጠረው።

አገር ሰው ከሌለባት ምንም ናት። ሰው አገር ከሌለው ምንም ነው። አገርና ሰው፣ ሰውና አገር የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጾች ናቸው። ሰው በአገር .. አገር በሰው ነው የሚከበሩት። አገር በሰላም ካልሆነ በምንም አትቆምም። ሰው በሰላም ካልሆነ በምንም አያምርም። ሰላም ስናጣ፣ አንድነት ሲርቀን የአገራችንን መሰረት እየነቀነቅን ነው።

ተነጋግሮ መግባባት ሲያቅተን፣ ተቻችሎ መኖር ሲከዳን የአገራችንን መሰረት እየገፋን ነው። በእኛ ሰላም ማጣት ከእኛ ውጪ የሚጎዳ ማንም የለም። ሰላም ባጣንባቸው ሁለት ዓመታት ውስጥ ሁሉንም አይነት መከራ አይተናል። አሁን ስለሰላም የምንጮህበት ጊዜ ነው.. አሁን የመጣው ሰላም እንዲቀጥል የምንታገልበት ጊዜ ነው።

ኢትዮጵያን እንስራ። ብዙ ሆና ያነሰችውን፣ እልፍ ሆና የጎደለችውን ሀገራችንን እንታደግ። ሰው ሳታጣ ሰው ያጣችውን፣ ሃሳብ ሳታጣ ሃሳብ ያጣችውን አገራችንን እንማግር። ታሪክ ሞልቷት ታሪክ ያጣችውን አገራችንን እናድስ። በሰላሙ ዋዜማ ጥላቻ የሞላቸው አሮጌ አቆማዳዎቻችን በአዲስ እንተካ ።

የፖለቲካ እድፍ ያቆሸሻቸው ትርክቶች በምክንያታዊ ሃሳቦች መሞላት አለባቸው። ከእንግዲህ ጭንቅላቶቻችን የመፍትሄ ሃሳብ እንጂ የጦርነት ሃሳብ ማማጣቸው ይበቃል። ከእንግዲህ ልቦቻችን የይቅርታና የፍቅር ቦታ እንጂ የመለያየት ቦታ መሆናቸው ያበቃል። ከእንግዲህ ጀርባዎቻችን በጥላቻ መጉበጥ የለባቸውም።

ከእንግዲህ ፖለቲከኞቻችን የእርቅ ሃሳብ እንጂ በመለያየት ሃሳብ ጊዜ ማጥፋት የለባቸውም። ከእንግዲህ በሚያግባቡንና በሚያስተቃቅፉን የጋራ ጉዳዮቻችን ላይ እንምከር። ከእንግዲህ ኢትዮጵያን ከፍ በሚያደርጉ ተግባራት ላይ እንሳተፍ። በሰላማዊ ተግባቦት ዝቅ ያለችውን አገራችንን ከፍ ማድረግ ይጠበቅብናል። በአገራዊ ምክክር አዲስና ነባር ችግሮቻችንን እየቀረፍን ሰንኮፏን የጣለች ኢትዮጵያን እንውለድ።

# ፈረሶች እና ፈረሰኞች

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

በጥንታዊት ግሪክ አሥር ዓመት ጦርነት ተካሂደ። በግሪክ እና ትሮይ መካከል ። ግሪኮች ጦርነቱ ሰለቻቸው ፤ እጅ መስጠት አልፈለጉም። እናም መላ ዘየዱ። ግዙፍ የጣውላ ፈረስ ሠርተው ውስጡ ምርጥ ወታደሮችን አስቀምጠው ሸሹ። ግሪኮች ሲሸሹ ትሮዮች በድል ሰከሩ። ትሮዮች ለድላቸው መታሰቢያ እንዲሆን ፈረሱን ጎትተው ከተማቸው መሐል አቆሙ። በውድቅት ሌሊት፣ ፈረሱ ውስጥ የተደበቁት ግሪኮች ወጥተው የትሮይ ከተማን በማውደም በጦርነቱ አሸናፊነት ተቀዳጁ። እናም ባልተጨበጠ ድል የሰከሩ ትሮዮች በተሸናፊነት ከሰሩ። የትሮይን ፈረስ ያነሳነው ነገርን ነገር ያነሳዋን ብለን ነው። ስለኢትዮጵያ ፈረሶችና ፈረሰኞች ልናወጋችሁ ሽተን ።

የሰው ልጅ ፈረስን ለማዳ አድርጎ መጠቀም የለመደው በ3 ሺ ዓ.ዓ መሆኑ ን ሰነዶች ያሳያሉ። የፈረስ የእድሜ ጣሪያ ከ25 እስከ 30 ዓመት ሲሆን በዓለም ከ3 መቶ በላይ ዝርያዎች ለልዩ ልዩ አገልግሎት ይረባሉ። በኢትዮጵያ ስምንት የፈረስ ዝርያዎች እንዳሉ መረጃዎች ያሳያሉ። በዋናነት የሚጠቀሱት የፈረስ ዝርዎች የሰላሌና (በጋላቢነታቸው) የቦረና ፣ እንዲሁም የሶማሌ ጅግጅጋ አለፍ ብሎ የሚገኝ ዋልዌል የዐረብ ዝርያ ያላቸው ፈረሶች ናቸው። የባለሥልጣናት ጉብኝት በገጠር አካባቢዎች ሲኖር ገበሬዎች በብዛት በባህላዊ ጭፈራና ኮርቻ ባጌጠ ፈረስ አቀባበል ማድረግ በኢትዮጵያ የተለመደ ነው። ይህ አሁንም ይታያል። ፈረሶች በአገራችን በወይና ደጋ፣ ደጋና ቆላና ሥፍራዎች ይኖራሉ።

ፈረስ ከጋማ ከብቶች አንዱ ነው። በጀርባው ኮርቻ ጭኖ ሰው የሚቀመጥበት ። የሚወልዱ ፈረሶች ባዝራ ፤ወንዱ ደግሞ ድንጉላ ይባላል። ፈረሰኞች በፈረስ የሚጋልቡ ፤ ግልቢያ አዋቂዎች ማለት ነው። ፈረስ ዘበኛ ማለትም ፈረስ የሚጠብቅ ፤ ባልዳራስ ጭፍራ ፤የንጉሥ ፈረስ ጠባቂ ማለት ነው። ሰዎች ፈረስ እየጋለቡ ሩቅ ቦታ መሄድ ሲፈልጉ ኮርቻ ይጠቀማሉ። ኮርቻ በበቅሎ፣ በፈረስ ጀርባ ላይ ተደርጎ የሚታሠርና ሰው የሚቀመጥበት ከእንጨትና ከቆዳ የሚሠራ ዕቃ ነው። በቅሎ እና ፈረስ በብዛት የኮርቻ ከብት ይባላሉ። ይህም ለኮርቻ ጭነት ብቻ የተመደበ፣ በብዛት ሰው የሚጓጓዝበት በመሆኑ ነው።

ኮርቻ ከላይ እንደተገለፀው መቀመጫ ሆኖ ከፊት መያዣ ያለው ቀዳማይ ሲባል፤ የኋላ መደገፊያው ደኅራይ ይባላል። መወጣጫው እግር የሚጠልቅበት ብረት ርካብ ፤ ከጅራቱ ሥር የሚገባው የጨርቅ ትልታይ ወይም በለስላሳ ቆዳ የተሸፈነ ጠፍር ወዴላ ይባላል። ፈረሱን አቅጣጫ ለመምራት ፍጥነቱን ለመቀነስ የሚረዳው ከቆዳ የሚሠራው ልጓም ነው። ልጓም የመሪ ዓይነት ሚና አለው። ፈረሰኛው አለንጋንም ይጠቀማል።

ኢትዮጵያ በፈረሰኞች በዓለም ትታወቃለች። ነፃነቷን አስከብራ፣ የነጮችን ወራራ አሳፍራ የኖረችው በዘመኑ በነበራት ፈረሶችና ፈረሰኞች ነው። ንግሥት ሳባ የሰሎሞንን ጥበብ ከኢትዮጵያ ለማየት የሄደችው በፈረስና በግመል ነበር። አሁን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ገዳም የሆነው በእስራኤል የዴር ሱልጣን ገዳም በዘመኑ የንግሥት ሳባ ፈረሶች ማረፊያና ማሰሪያ እንደነበር ይነገራል።

በኢትዮጵያ ጀግኖች መሳፍንት መኳንንት ነገሥታት ዜጋው ሁሉ በፈረስ የመቀመጥ ልምድና ባህል ነበራቸው። በዘመኑም በጨዋ ልጅ አስተዳደግ አንደኛ ደረጃ ክብርና ማዕረግ የሚያሰጥ እንደነበር የሰዋስው ድረገፅ ያስረዳል።

በጎንደር በፋሲል ግቢ የሚገኝ በዐፄ በካፋ የተሠራ የፈረሶች መኖሪያ ህንጻ ነበር። የዞብል ፈረስ መቃብርም አለ። መቃብሩ ከፋሲል መዋኛ አጠገብ ይገኛል። ዞብል በአንዳንዶች ዘንድ ተወዳጁ የዐፄ ፋሲለደስ ፈረስ መሆኑ ይታመናል። ሌሎች ግን የልጃቸው የቀዳማዊ ዮሐንስ ፈረስ ነው ይላሉ። ሆነም ቀረም የዞብል መቃብር በክብ ቅርጽ የተሠራ መታሰቢያ ነው። በግሌ ቦታውን ባላየውም ከቆይታ ብዛት ጉዳት እየደረሰበትና ዛፎች በመካከሉ እየበቀሉበት እየፈረሰ ያለ ምናልባት ብቸኛው የኢትዮጵያ ፈረስ መዘክር የሚሆን ነው። ያም ሆነ ይህ የፈረሱን መቃብር የሠሩለት ፈረስ በዘመኑ ክብር የሚሰጠው መሆኑን የሚያመላክት ነው።



በኢትዮጵያ ካሏት ግዙፍ የባህል ሀብቶች መካከል በሁሉም የኢትዮጵያ አካባቢዎች ዘንድ የሚታወቀው የሚዘወተረው የፈረስ ጉግስ ነው። የቆየ ታሪክ ያለውና ትልቅ ባህላዊ እሴት የሆነ በፈረስ የሚደረግ ውድድር ወይም ጨዋታ ነው። ጉግሥ ሁለት ዓይነት ሲሆን፣ አንደኛው ከአንድ ቦታ ተነስቶ ወደ ሌላ ቦታ የሚደረግ ሽምጥ ግልቢያ ነው።

ሁለተኛው ጋሻና ጦር በመያዝ ሽምጥ እየጋለቡ አባራሪና ተባራሪ እየሆኑ ተወዳዳሪውን ጋሻ አልፎ ለመውጋት ወይም ለመማረክ የሚደረግ የጨዋታ ፍልሚያ ነው። ጦር የሚባለው በጦር ምትክ የሚያዝ ዘንግ ነው። ይህም በክፉ ጊዜ አገርን ከጠላት ወረራ ለመከላከል ጭምር የረዳ ነው። የፈረስ ጉግስ ወታደራዊ ብቃትና ጀግንነት የሚለካበት ነበር። በፈረስ ጉግሥ ተወዳድሮ ያሸነፈ «ፈረሰኛ» የሚል ማዕረግና የፈረሰኛ መሬት በሽልማት ይሰጠው ነበር። በዘመናችን ፈረሰኛ የሚባለው አውዳሚው ነው። (በክረምት ወንዝ ድንገት ሲሞላ ፈረሰኛ ይባላል፤ ተሻጋሪውን ይወስደዋል።) በጥንቱ ኢትዮጵያዊ ባህል ዜጋው የፈረስ ጉግሥ ጨዋታና የግልቢያ ችሎታ ማወቅ ግድ ነበር። በአገራችን ፈረስ የአሸናፊነት ምልክት የክብር መገለጫ ነገሥታቱ ጀግኖቹ ዜጎቹ እንደ ልጅ ይጠሩባቸው ነበር።

በአገራችን ባህል ለሰዎች የሚሰጠው የፈረስ ስም የሰውየውን ጠባይ ሁኔታ ምኞትን ጭምር አጠቃሎ የሚይዝ ሠፊ ትርጉምና መግለጫ የያዘ ነው። ቅጽሉ ስሙ የሚሰጠው ለፈረሱ ቢሆንም፤ የባለቤቱን ሙያ የሚገልጽና የሚያሞግስ ሰውየውንም የሚያኮራ ነው። በሰላም፣ በአስተዳደር ፣በዳኝነት፣ በምክር፣ በጦርነት ጊዜ በጀግንነትና በዘዴ የሚያሳየውን ደግነትና ርህራሄ ኃይልና ቅልጥፍና ከባልደረቦቹ ወይም ከሌሎች የሚሰጠው መታወቂያ ነው።

ከፈረስ ስም መካከል አስተዳደርንና ዳኝነትና የሚያመለክቱ ኣባ ዳኘው፣ መቻል፣ ይርጋ ፤ ለጋስነትንና ችሮታን የሚያመለክቱ አባ ባህር፣ ለጋስ፣ ሙላት፣ ቁጡነትን ጀግንነትን የሚያመለክቱ አባ ቃኘው፣ ደፋር ፣ መብረቅ የፈረሶቹን ቀለም የሚያመለክቱ አባ ጉራች ፣ ሻንቆ፣ ዳማ ትክክለኛነትን የሚያመለክቱ አባ ሚዛን ፣መልዐክ ፤መስፋፋትንና ዕድገትን የሚያሳዩ አባ ይትረፍ፣ ደርብ ወዘተ ይጠቀሳሉ።

የተባበሩት መንግሥታት ዓለም የእርሻ ድርጅት በፈረንጆቹ በ2017 ባወጣው የስታትስቲክስ መረጃ ፤ ኢትዮጵያን ፈረስ ከሚያረቡ አገሮች ስምንተኛ ደረጃ ላይ ያስቀምጣታል። ይህም ከዓለም አስር ቀዳሚ ሀገሮች ተርታ ይመድባታል። በፈረስ ብዛት አገራችንን ፤ዩናትድ ስቴትስ አሜሪካ፣ ሜክሲኮ፣ ቻይና፣ ብራዚል፣ ሞንጎልያ፣ አርጀንቲናና ካዛኪስታን በቅደም ተከተል ይመሩዋታል። ሩሲያና ኮሎምቢያ ደግሞ ኢትዮጵያን ይከተልዋታል። የዊኪፒዲያ ድረገፅ የተባበሩት መንግሥታት ምግብና እርሻ ድርጅት በ2016 ያወጣውን መረጃ ጠቅሶ እንዳሠፈረው በአፍሪካ ከኢትዮጵያ ቀጥሎ ፈረስ በማርባት ቻድና ግብፅ በሁለተኛና ሦስተኛ ደረጃ ይከተላሉ። በኢትዮጵያ ያሉት ፈረሶች ብዛት 2 ነጥብ 8 ሚሊዮን በላይ ሲገመት ይህም የአፍሪካን ፈረሶች ሩብ (1/4 ኛ) ያህል ነው።

ሃይማኖታዊና ባህላዊ በዓላትን ስናስብ ኢሬቻ፣ ፊቼ ፣ጨምበላላ፣ የጥምቀት ከተራና የመስቀል ደመራ የቃና ዘገሊላ በዓል የሚያምሩት የሚደምቁት በፈረሶችና ፈረሰኞች ሲታጀቡ ነው። ከ80 ዓመት በላይ የዘለለ ምሥረታ ያለው የአገው ፈረሰኞች ማኅበርም በየዓመቱ ጥር 23 ቀን ፈረሳቸውን በኮርቻ አጊያጊጠው የፈረስ ፌስቲቫል ያከብራሉ። ፈረሰኛ የማህበሩ አባል ለመሆን፣ ለፈረሱ ኮርቻ፣ ፋርጌሳ፣ ለኮ፣ ወዴላ፣ ውስጠ ምቹ እና ግላስ የተባሉ መሉ መሣሪያዎች ማሟላት ሲኖርበት፣ ለራሱ ደግሞ አለንጋ፣ ዘንግ ገምባሌ፣ ባት ተሁለት ሱሪ፣ ሳሪያን ኮት እና ጀበርና ማሟላት ይጠበቅበታል። የፈረስ በዓሉ የሚዲያ ሽፋን ካገኘ ወደፊት የቱሪስት መስህብ ይሆናል። በተባበሩት መንግሥታት የባህልና የሳይንስ ድርጅት የመመዝገቡ ዕድሉም ሠፊ ይመስለኛል።

በፈረሰኝነት የሚታወቁት ኦሮሞዎችም በመህል አገሪቱ ይሄን ሺጋ ባህል ለማሻገር መጣር አለባቸው። ባለፈው ጥር ወር በኦሮሚያ ክልል ሰንዳፋ ከተማ «ባሕላዊ የፈረስ ፌስቲቫል ለቱሪዝም ልማት» በሚል መሪ ቃል የፈረስ ስፖርት ፌስቲቫል መካሄዱን አስታውሳለሁ። በወቅቱ በኢትዮጵያ ታሪክ የኦሮሞ ፈረሰኞች በአገር ግንባታ ላይ ትልቅ ሚና እንደነበራቸው ተወስቷል። በዝግጅቱ ከኦሮሚያ ክልል ልዩ ልዩ ዞኖች የተውጣጡ ፈረሰኞች የፈረስ ጉግስ፣ ሽምጥ ግልቢያ እና ባሕላዊ ጭፈራዎችን አቅርበዋል። በተጨማሪም በፌስቲቫሉ ላይ ከሌሎች ሕዝቦች ጋር ሆነው ኢትዮጵያን ያጸኑ የኦሮሞ ጀግና ፈረሰኞች ተዘክረው ነበር።

ፈረስ ጉግሥ በሁሉም የኢትዮጵያ አካባቢዎች የተለመደና የሚዘወተር ባህላዊና ጥንታዊ ጨዋታ ነው። በማንኛውም ጊዜ የሚከናወን ጨዋታ ቢሆንም በውድድርና በትርዒት መልክ የሚቀርበው በዓላትን ተንተርሶ ነው። በመስቀል ደመራ በጥምቀት ከተራ በገና በልዩ ድምቀት ይከናወናል። በመስቀል ልጃገረዶች አንድ ላይ ሆነው ሲዘፍኑ ወጣት ወንዶች በበኩላቸው ለዚህ ብለው ሲቀልቡዋቸው እና ሲገሩዋቸው የከረሙትን ፈረሶቻቸውን ይዘው በመምጣት ለጉግሥ ውድድር ይሰለፋሉ። በጥምቀት በተለይ በቃናዘገሊላ እለት ታቦት ካስገቡ በኋላ የፈረስ ጨዋታቸውን ይቀጥላሉ። በልደትም በየመስኩ የጉግሥ ጨዋታ የተለመደ ነው ።

ተሽከርካሪ ከመጣ በኋላ ፈረሶች በከተሞች ተፈላጊነታቸው እየቀነሰ መጣ። ሆኖም በከተሞች አልፎ አልፎ ፈረስን የመጠቀም ልምድ አለ። በአነስተኛ ከተሞችና በአዲስ አበባ ከተማ ዳርቻዎች የጋሪ ፈረስን መጠቀም ተጀመረ። የጋሪ ፈረሶች ግራና ቀኝ የሚያየው ዓይናቸው በቆዳ ነገር ተከልሎ በአንድ አቅጣጫ እንዲያይና እግራቸው ወይም ኮቴያቸው ላይ ብረት እንደጫማ ተመቶ እንዲያለግሉ ይደረጋል። ለጋሪ ፈረስ ግንባሩ ላይና አፍንጫው ላይ የሚደረገው ቆዳ ፋሎ ፤የሰዎች መቀመጫው ኮርቻ፣ መደገፊያ ጀርባው ሌቤቻ፣ ደረቱ ላይ የሚወጠረው ቅናት፣ ከተሽከርካሪ ጎማው እስከ ደረቱ የሚደረሰው ግራና ቀኝ ያለው እንጨት ስታንጋ፣ ጎማዎቹን የሚያይዘውና የሚደግፈው ባሌስትራ ይባላል።

በዓለም ለማዳ ያልሆኑ ፈረሶች (feral horses) በተወሰኑ አገሮች ይገኛሉ። በአሜሪካ አትላንቲክ ጠረፍ፣ በአውስትራሊያ ፣ በፖርቱጋልና ስኮትላንድ ይገኛሉ። የአውሬነት ፀባይ ስላለባቸው የዱር ፈረሶች ይባላሉ። በአፍሪካ በናሚቢያ ብቻ ይገኛሉ ቢባልም በኢትዮጵያም በምሥራቅ ሐረርጌ የዱር ፈረሶች ተገኝተዋል።

ዶ/ር ከፈና ኢፋ በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የሆለታ ግብርና ምርምር ማዕከል ዳይሬክተር ናቸው። ከአዲስ አበባ 565 ኪሎ ሜትር ርቆ በምሥራቅ ሐረርጌ በጃርሶና ጉርሱም ወረዳ መካከል በሚገኘው በቁንዱዶ ተራራ በተገኙ ዱር ፈረሶች ላይ ጥናት አድርገዋል።

የቁንዱዶ ተራራ ሰንሰላታማና ከ3 ሺ ሜትር በላይ ከፍታ ያለው ነው። ለፈረሶቹ ተራራውን መውጣት አስቸጋሪ ነው። ፈረሶቹ በተራራው ከመቶ ዓመታት በላይ እንደኖሩበት ጠቁመዋል። ከአስር ዓመት ወዲህ ባደረጉት ጥናት ሰባት የሚደርሱ ፈረሶች ብቻ ቀርተው ነበር። በሥፍራው ያለ ጫካ በሰው እየተመነጠረ አውሬው (ጅብ፣ አነርና ነብር) እየሸሸ ፈረሶቹንም እያደነ ሲበላ፤ ሰውም ለቤት እንስሳነት ለማደን ሲጠቀም ነበር። የኢትዮጵያ ብዙሃ ሕይወት ኢንስቲትዩት ፣ የሀሮማያ ዩኒቨርሲቲና የኦሮምያ አካባቢ ደን ባለሥልጣን የመግባቢያ ስምምነት አድርገው ለአስር ዓመታት በሠሩት ሥራ ሰባት ብቻ ሆነው ዝርያቸው እየጠፉ የነበሩት የዱር ፈረሶች 35 ደርሰዋል።

የቁንዱዶ ፈረሶች እየተራቡ (ሲባዙ) ሲሄዱ ኢትዮጵያን በአፍሪካ ብቸኛው የዱር ፈረስ መገኛ እንደሚያደርጋት ዶ/ር ከፈና ኢፋ የሰጡት መረጃ ያስረዳል። ይህም እንደ ዋልያ፣ ኒያላ፣ ቀይ ቀበሮ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኝ የዱር ፈረስ ያደርጋታል ሲሉ ይገልፃሉ። በናሚቢያ ይገኛል የተባለው የዱር ፈረስ በ 17ኛው ክፍለ ዘመን በቅኝ ወራሪዎች ትተውት የሄዱት እንደሆነም ያስረዳሉ። የቁንዱዶ የዱር ፈረሶች ለማዳ ፈረሶች በማይገኙበት በምሥራቅ ሐረርጌ መገኘታቸው ፤ተራራው ቀዝቃዛማና አስቸጋሪ መሆኑና እንዴት ሊወጡ እንደቻሉም ትንግርት መሆኑን ጠቁመዋል። ቀስ በቀስ ቦታው የቱሪስት መስህብ የሚሆን ነው።

ፈረሶች አገልግሎታቸው ዘርፈ ብዙ ነው። ፈረስና አህያ አገልግለው እርጅና ሕመም ሲያጋጥመው እንደ አሮጌ ቁና ሜዳ ላይ የመጣል ልምድ በሀገራችን አለ። የግብርና ምርምርና የሚመለከታቸው አካላት መላ ቢፈልጉለትና የሕክምና ማዕከላት ቢኖሩ ጥሩ ነው። ባህላዊ የፈረስ ኮርቻ እየተረሳ እንዳይመጣም በፖሊስ ፈረሶች በቤተመንግሥት ፈረሶች ጭምር ብሔራዊ በዓል ሲሆን በኮርቻው ደምቀው አጊጠው ሲገለገሉ ቢታዩ ሽጋ ነው።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

# ክፍተቱን ለመሙላት የሚጥሩ ወጣቶች

አስናቀ ፀጋዬ

ጓደኛሞች ናቸው። በተማሩበት የጤና ባለሞያ ትምህርት ዘርፍ በመንግሥት ጤና ተቋማት እያገለገሉ ይገኛሉ። በየተቋማቸው መደበኛ የሕክምና ሥራቸውን ሲያከናውኑ ከብዙ ታካሚዎች ጋር ይገናኛሉ። ታካሚዎች ሕክምና ፈልገው ሲመጡ ከገጠማቸው የጤና ችግር በተጓዳኝ የአእምሮ ህመም ሲያጋጥማቸው ያያሉ። ለአንዳንዶቹ የአእምሮ ታማሚዎችም ምክር ቢጤ ይሰጣሉ።

በዚሁ አጋጣሚም ወደጤና ተቋም ለሕክምና መጥተው የአእምሮ ህመም የሚያጋጥማቸው ታካሚዎች ራሱን የቻለ ሕክምናና የምክር አገልግሎት እንደሚያስፈልጋቸው ተረዱ። ይህንኑ ሃሳባቸውን ወደተግባር በመለወጥ የእርዳታ ድርጅት አቋቁመው የአእምሮ ህመም የሚያጋጥማቸው ሰዎች ምስጢራቸው ተጠብቆ የምክር አገልግሎት የሚያገኙበትን መንገድ አመቻቹ። አሁን ደግሞ በአእምሮ ህመም ምክንያት ጎዳና ላይ የወደቁ እናቶችንና ሕፃናትን ለማንሳት ሥራዎች ጀምረዋል። የብሩህ ሕይወት እርዳታ ድርጅት መሥራች ወጣቶች።

ሲስተር ነፃነት ሙሉ የብሩህ ሕይወት እርዳታ ድርጅት መሥራችና የሕዝብ ግንኙነት ናት። በሞያዋ ነርስ ስትሆን በካውንስሊንግ ሳይኮሎጂ የመጀመሪያ ዲግሪ አላት። በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ጤና ጣቢያ ውስጥ ትሠራለች። በአእምሮ ጤና ማማከር ሥራ ላይ ያተኮረ የእርዳታ ድርጅት የማቋቋሙ ሃሳብ በእርሷና ጓደኛዋ ከሁለት ዓመት በፊት ነበር የተጀመረው። ሁለቱም ጤና ዘርፍ ላይ እንደመሥራታቸው በሀሳቡ ላይ ብዙ አውርተውበታል። ታካሚዎች ከሚያገኙት ሕክምና አገልግሎት በተጨማሪ በሽታቸው ሳይታወቅ በተደጋጋሚ የሚመላለሱ እንዳሉም አይተዋል። ትንሽ ጊዜ ሰጥተዋቸው ሲያወሯቸው ህመሙ የሥነ ልቦና ጉዳትና ከአእምሮ ጋር የተያያዘ ችግር እንደሚገጥማቸው ተረድተዋል። ከሕክምናው በተጓዳኝ ጥቂት ምክሮችን ሲለግሷቸው ለውጥ ሲያሳዩ ተመልክተዋል።

በዚህም በአእምሮ ህመም ላይ ብዙ መሥራት እንዳለባቸው ሲያወሩ ቆዩ። በተለይ ደግሞ በሚሠሩበት ጤና ጣቢያ የምትታከም አንድ እናት በተደጋጋሚ እየታመመች ስትመላለስ የሥነ ልቦና ሕክምና አድርገውላት ተሽሏት ወደቤቷ ስትሄድ ከመደበኛ ሕክምና አገልግሎት ጎን ለጎን የሥነ ልቦናና የአእምሮ ህመም ሕክምና ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ተረድተዋል። በተለይ ደግሞ የአእምሮ ጤና የሁሉም የሰውነት ጤና መሠረት እንደሆነ ለመገንዘብ ችለዋል።

በዚህ መካከል እርሷና ጓደኛዋ አንድ ሌላ የሕክምና ባለሞያ በመጨመር በወጣቶች ዙሪያ ከሚሠራ አንድ ድርጅት ጋር በመሄድ በሥራ ፈጠራ ውድድር ላይ ሃሳቡን ይዘው ቀረቡ። በውድድሩ የያዙት ሃሳብ ወደ እርዳታ ድርጅት ቢቀየር የሥነ ልቦናና የአእምሮ ህመም ሕክምናና ምክር አገልግሎቱን ይበልጥ ተደራሽ እንደሚሆን ተነገራቸው። ሃሳባቸውም አሸናፊ ሆኖ ፍቃድ የማውጣቱንና ሌሎች ሥራዎችን መሥራት ቀጠሉ።

ሁሉም ሰው የተሟላ የአእምሮ ጤና አለው ማለት አይቻልም። የሁሉም ሰውነት ጤና መሠረቱም የአእምሮ ጤና ነው። የአእምሮ ጤና በቀላሉ ሊጠበቅ የሚችል ቢሆንም ካልተጠበቀ ከባድ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል። አንዳንድ ሰዎች አእምሯቸው ጤነኛና የስኳር ታማሚ ሆነው ራሳቸውን እያከሙ ሕይወታቸውን ዘላቂ ሊያደርጉ ይችላሉ። ነገር ግን ደግሞ አእምሮውን የታመመ ሰው ምንም ዓይነት የጤንነት ችግር ባይኖርበት እንኳን በየትኛውም መስክ ውጤታማ ሊሆን አይችልም።

እነርሱም በአእምሮ ጤና ላይ ለመሥራት የፈለጉት በዚህ ምክንያት ነው። በተለይ ደግሞ ባለፉት ሁለት ዓመታት የተከሰተው ጦርነት በብዙ መልኩ የፈጠረው ጫና የሰዎችን አእምሮ ጤናን በብዙ የሚጎዳ መሆኑን በመረዳት በአእምሮ ጤና ላይ ለመሥራት ይበልጥ ተገፋፍተዋል። በመቀጠል ስልክ ቁጥራቸውን በካርድ አሳትመው በመበተን ከመደበኛ ሥራቸው



ዶክተር ትዝታ አለሙ፤



ዶክተር እሱባለው አብርሃም



ሲስተር ነፃነት ሙሉ፤

ጎን በአእምሮ ህመም ዙሪያ በስልክ የማማከር አገልግሎት በነፃ መስጠት ጀምረዋል። ተጠቃሚዎችም ስልካቸውን ለሌሎች በማጋራት እንዲደውሉላቸው በማድረግ ተጨማሪ የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎችን ቁጥር ማሳደግ ችለዋል። ይህም አሠራር ተጠቃሚዎች ምስጢራቸው ተጠብቆ አገልግሎቱን እንዲያገኙ አስችሏል። የምክር አገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ቁጥር ሲበዛ ደግሞ ተጠቃሚዎቹን በአካል በማግኘት አገልግሎቱን እንዲያገኙ እያደረጉ ነው። የምክር አገልግሎቱን ይበልጥ ለማዘመንና የአእምሮ ሕክምና የምክር አገልግሎቱን ለሁሉም ተደራሽ ለማድረግ መተግበሪያ የማበልፀግ ሥራም እየሠሩ ይገኛሉ።

በዚህም አገልግሎቱን ፈልገው ወደ እጅ ስልካቸው የሚደውሉ ሰዎች ቁጥር ከፍተኛ መሆኑን ማረጋገጥ ችለዋል። የምክር አገልግሎቱን ያገኙ ሰዎች መረጃውን ለሌሎች በማጋራት ደውለው አገልግሎቱን እንዲያገኙም አስችለዋል። አገልግሎቱ ውስን መሆኑና ለሌላው ሰው በበቂ ሁኔታ እንዳልደረሰ አመላክቷቸዋል።

ምንም እንኳን ወጣቶቹ ከመደበኛ ሥራቸው ጎን ለጎን የምክር አገልግሎቱን በነፃ እየሰጡ የሚገኙ ቢሆንም ተቋማቸው የእርዳታ ድርጅት እንደመሆኑ በአእምሮ ህመም ምክንያት ጎዳና ላይ የወደቁ እናቶችንና ሕፃናትን የማንሳት እቅድ ስላላቸው ይህን ሊደግፍ በሚችል መልኩ የተወሰነ ክፍያ ሊኖረው የሚችልበትን አሠራር የመዘርጋት እቅድ አላቸው። በቀጣይ የነፃውንም ሆነ የክፍያውን የምክር አገልግሎት እኩል ለማስኬድም ሃሳብ አላቸው።

የድርጅታቸው ተቀዳሚ ዓላማም ሰዎች ስለ አእምሮ ጤና ግንዛቤ ኖሯቸው ህመሙን አስቀድመው እንዲከላከሉ ማድረግ ነው። የማማከር አገልግሎቱንም በስፋት ለማህበረሰቡ ተደራሽ ማድረግም የድርጅቱ ሌላኛው ዓላማ ነው። የማስተማር፣ ስልጠናዎችን የመስጠትና ሰዎች የአእምሮ ጤና ተገንዝበው ራሳቸውን በመጠበቅ ምርታማና ውጤታማ እንዲሆኑ የማድረግ ሥራም ድርጅቱ ይሠራል።

ሲስተር ነፃነት እንደምትለው በአሁኑ ጊዜ ድርጅቱ በጥቅምት ወር 2015 ዓ.ም ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሕጋዊ ሰውነት አግኝቶ የራሱን መዋቅር ዘርግቶ የአእምሮ ሕክምና ምክር አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። በዚሁ መዋቅር መሠረት በአእምሮ ጤና ዙሪያ ሥልጠና የሚሰጡና የማማከሩን ሥራ የሚሠሩ ሰዎች አሉት። የራሱ ሥራ አስኪያጅ፣ ገንዘብ ያዥ አለው። እነዚህ ሰዎች ግን ከመደበኛ ሥራቸው ጎን ለጎን ሥራውን የሚያከናውኑት በነፃ ነው።

ድርጅቱ በተወሰኑ አካባቢዎች ላይ ብቻ ታጥሮ መሥራት አይፈልግም። ከዚህ ይልቅ በአእምሮ ጤና ላይ እንደአገር መሥራት ይፈልጋል። ሁሉም ሰው የአእምሮ ጤናው እንዲጠበቅ፣ የአእምሮ ጤናን በሚመለከት

**አንድ እናት በተደጋጋሚ እየታመመች ስትመላለስ የሥነ ልቦና ሕክምና አድርገውላት ተሽሏት ወደቤቷ ስትሄድ ከመደበኛ ሕክምና አገልግሎት ጎን ለጎን የሥነ ልቦናና የአእምሮ ህመም ሕክምና ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ተረድተዋል**

በሰዎች ዘንድ ያለው ግንዛቤ እንዲሰፋ ፍላጎቱ አለው። ከዚህ አኳያ መንግሥትም ጉዳዩን ተረድቶ በተለይ የመሥሪያ ቦታ ማመቻቸት ይጠበቅበታል።

በአሁኑ ጊዜ ድርጅቱ ይህን መልካም ተግባር ቤት ተከራይቶ ለመሥራት ከፍተኛ ገንዘብ እየተጠየቀ ነው። በዚህም ምክንያት በድርጅቱ ውስጥ ያሉ የሕክምና ባለሞያዎችና ሌሎችም ባሉበት ቦታና በየቤታቸው ሆነው ሥራውን በነፃ እያከናወኑ ይገኛሉ። ከዚህ አንፃር ድርጅቱ መሥሪያ ቦታ ከመንግሥት ቢያገኝ በተለይ በአእምሮ ህመም ምክንያት ጎዳና ላይ የወደቁ እናቶችንና ሕፃናትን አነሳለሁ ብሎ ለያዘው ትልቅ ራእይ እውን መሆን አስተዋፅዖው የጎላ ነው።

ድርጅቱ በመነሻነት እናቶችን ከጎዳና ላይ ማንሳትና በአንድ ማዕከል ሆነው የሚረዱበትንና እንክብካቤ የሚያገኙበትን መንገድ የመቀየስ ውጥን ይዟል። ከዚሁ በተጓዳኝ በጎዳና ላይ የወደቁ ሕፃናትም እርዳታ የሚያገኙበትን ሁኔታ የመፍጠር ሀሳብ አለው። በተለይ ደግሞ ሕፃናቱ ከጎዳና ሕይወት ወጥተው ትምህርታቸውን በሚገባ ተከታትለው ውጤታማ ማድረግ ትልቁ ህልሙ ነው።

በሲስተር ነፃነት ሙሉ፣ ዶክተር ትዝታ አለሙና ዶክተር እሱባለው አብርሃም የሚመራው ብሩህ ሕይወት እርዳታ ድርጅት በስሩ ገንዘብ ያዥ፣ አስተዳደሮች፣ የማህበራዊ ጉዳይ ባለሙያዎች (ሶሻል ወርከሮችን) እና በጎ ፍቃደኛ ወጣቶችን አቅፏል። የአእምሮ ህመም ሕክምና ማማከር ሥራው ግን በሦስቱ ወጣቶች በነፃ ይከናወናል። ለዚሁ የማማከር ሥራ የሚረዳቸውን ትምህርትም ተከታትለዋል።

በቀጣይም ድርጅቱ በተለይ በአእምሮ ህመም ምክንያት በየጎዳናው ወድቀው የሚገኙ እናቶችን ከነልጆቻቸው በማንሳት በአንድ ማዕከል ሆነው ድጋፍና እንክብካቤ የሚያገኙበትን መንገድ ለማመቻቸት እቅድ ይዟል። በዋናነት ደግሞ ጤናማ አእምሮ ያለውና ምርታማነትን መጨመር የሚችል ትውልድ የመፍጠር ሀሳብም አለው።

ድርጅቱ ሕጋዊ ሰውነት አግኝቷል። ነገር ግን በቀጣይ በራሱ ቆሞ፣ ቢሮና ቋሚ አድራሻ ኖሮት የአእምሮ ሕክምና ማማከር አገልግሎቱ ለሁሉም ማህበረሰብ ተደራሽ የማድረግ እቅድም አለው። በዘርፉ ያሉ ባለሞያዎችን በማሳተፍ በአገር አቀፍ ደረጃ ጥሩ የሥነልቦና የማማከር አገልግሎት ማዕከል ሆኖ መገኘትም ይፈልጋል።

«የአእምሮ ጤና ችግር በጣም ሰፊ ነው» የምትለው ሲስተር ነፃነት ልክ እንደነርሱ ሁሉ ሌሎች ወጣቶችም በአእምሮ ጤና ምክር አገልግሎት ላይ በማተኮር እንዲሠሩና ኅብረተሰቡን እንዲጠቅሙ ጥሪ ታቀርባለች። በተለይ ደግሞ ከችግሩ አሳሳቢነት አንጻርና የአእምሮ ጤንነት የሁሉንም ተሳትፎ የሚጠይቅ እንደመሆኑ ሁሉም ወጣት ችግሩን ለመቀነስ ተደጋግፎና ተጋግዞ መሥራት እንደሚጠበቅበት ትጠቁማለች። ወጣቶች ብቻ ሳይሆን የሃይማኖት ተቋማትና ሌሎችም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት በጋራ ሊሠሩ እንደሚገባም ነው የምትጠቅሰው።

«እኛም በአእምሮ ጤና ላይ የምንሠራውን ሥራ አግዘውን መሥራት ለሚፈልጉ ማንኛውም የመንግሥትም ሆነ የግል ተቋማት በራችን ክፍ ነው» ትላለች ሲስተር ነፃነት። እስካሁን በመውደቅ መነሳት እዚህ የደረስን ብንሆንም በደንብ ወደፊት መራመድ እንድንችል በተለይ በአእምሮ ሕክምና ዘርፍ ያሉ ባለሞያዎች አብረውን ይሥሩ ስትል ጥሪ ታቀርባለች።

ድርጅቱ ገና ሥራውን እንደጀመረ ከመንግሥት በኩል የነበረው ምላሽ ብዙም አርኪ እንዳልነበር የምትናገረው ሲስተር ነፃነት፤ በሂደት ሥራው እየጎላ ሲመጣ ግን በጎ ምላሽ እያገኘ መሆኑን ትናገራለች። ነገር ግን አሁንም ቢሆን ለአእምሮ ጤና በመንግሥት በኩል ትኩረት ተሰጥቶበት ሊሠራበት እንደሚገባ ትጠቁማለች።

የአእምሮ ጤና ችግር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል። የኅብረተሰቡ ጤናም በዚሁ የአእምሮ ህመም በእጅጉ እየተፈተነ ነው። ይህም የአእምሮ ጤና ጉዳይ ምን ያህል ትኩረት እንደሚሻ ያሳያል። የአእምሮ ጤና ችግርን ለመቅረፍ መንግሥት በጥቂቱም ቢሆን ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ቢገኝም በቂ ነው ማለት ግን አይቻልም። እንደነ ነፃነት ያሉና በራሳቸው ተነሳሽነት በአእምሮ ጤና ላይ የማማከር አገልግሎት የሚሰጡ ባለሞያዎች የጀመሯቸው ሥራዎች እጅግ የሚያበረታቱ ናቸው። ነገር ግን የምክር አገልግሎቱን በስፋት ለማህበረሰቡ ለማዳረስና የአእምሮ ህሙማን በቋሚነት ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ ከመንግሥት በኩል በቂ ድጋፍ ሊያገኙ ይገባል።

# ሕገወጥ ንግድና የፀጥታ ስጋት የፈተነው የክልሉ ማዕድን ልማት አፈፃፀም

**ስምስም መንግሥቱ**

የማዕድን ልማት ለማኅበረሰብ የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ ምርቱ ለዓለም ገበያ ቀርቦ የውጭ ምንዛሪ በማስገኘትና ከውጭ የሚገባውን የማዕድን ውጤት በአገር ውስጥ በመተካት የምንዛሪ ወጪን በማስቀረት በአገር የምጣኔ ሀብት እድገት ላቅ ያለ ሚና እንዲወጣ ይጠበቃል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እምቅ አቅም ያለውን ይህን ዘርፍ በማነቃቃት ያለውን አበርክቶ ለማጉላት የሚያስችሉ ሥራዎችም በመንግሥት በኩል ሲከናወኑ ቆይተዋል። በተለይም በያዝነው በጀት ዓመት በዘርፉ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ በፌዴራልና በክልሎች ጭምር የንቅናቄ መድረኮችን በማዘጋጀት፣ በጥናትና ምርምር የታገዘ ሀብትን በመለየት፣ ዘርፉን ከፍ ባለ ደረጃ ለመምራት የአደረጃጀትና የመመሪያ ማሻሻያ እርምጃዎች በመውሰድ እንዲሁም ማዕድን ሚኒስቴር ከክልሎች ጋር የተናበበ ሥራ ለመሥራትና ሁሉም የየድርሻውን እንዲወጣ በማድረግ ረገድ ከተከናወኑት ተግባራት ተጠቃሽ ናቸው።

በዘርፉ ውጤት እንዲመዘገብ በበጀት አመቱ ከላይ የተነሱት ሥራዎች ቢከናወኑም ሕገወጥ ግብይትና የፀጥታ ስጋቶች ከፍተኛ ማነቆዎች ነበሩ። በተለይም ወደ ብሔራዊ ባንክ መግባት የነበረበት የወርቅ መጠን በከፍተኛ ሁኔታ ያሽቆለቆለው በዚህ ወቅት እንደሆነም መረጃዎች ያመለክታሉ። በጌጣጌጥ ማዕድን ዘርፍም ቢሆን በተለይም በዋጋ ውድና በዓለም ገበያ ተፈላጊ በሆኑት ላይ ሕገወጥ ግብይቱ መስፋፋቱም በተደጋጋሚ ሲነሳ ይደመጣል።

የዝግጅት ክፍላችን በዛሬው የምድር በረከት አምድ ላይ ሕገወጥ ግብይትንና የፀጥታ ስጋትን በመቋቋም እንደ ክልል እቅድን ለማሳካት ምን ተግባራት ተከናወኑ? ምንስ ውጤት ተገኘ? የሚለውን ርእሰ ጉዳይ ያነሳል። ዋንኛ ትኩረቱንም በኦሮሚያ ክልል ላይ አድርጎ ያለፉት 6 ወራትን የሥራ አፈፃፀም በመዳሰስ እንደሚከተለው አቅርበናል። መረጃውን ያደረሱን የኦሮሚያ ማዕድን ልማት ባለሥልጣን ኃላፊ አቶ ተስፋዬ መገርሣ ናቸው።

እንደ አቶ ተስፋዬ ገለጻ፤ የኦሮሚያ ማዕድን ልማት ባለስልጣን በበጀት አመቱ በእቅዱ ያስቀመጠው ዋና ግብ በአገራዊ ምጣኔ ሀብት ላይ አስተዋጽኦ ሊያበረክት የሚያስችል የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት አንዱ ሲሆን፣ ተኪ የማዕድን ውጤቶችን በማልማት የውጭ ምንዛሪ ወጪን ማስቀረት ሌላው ተልዕኮው ነው። ሦስተኛው ደግሞ በዘርፉ ለዜጎች ሰፊ የሥራ ዕድል እንዲፈጠር ማድረግ ነው። እነዚህን ተልዕኮዎች ይዞ ባደረገው እንቅስቃሴ በግማሽ በጀት አመት በአንዳንድ ተግባራቱ ላይ የሚያበረታታ፣ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ደግሞ ዝቅተኛ አፈፃፀም ለማስመዝገብ ተገዷል።

«በበጀት አመቱ የእቅድ ሥራ ውስጥ የፈቃድ አሰጣጥና አስተዳደር ሥራ ይገኝበታል» የሚሉት አቶ ተስፋዬ፤ የማዕድን ፈቃድ አዋጅን መሠረት በማድረግ በበጀት አመቱ በእቅድ የተያዘው ለ2ሺ115 አልሚዎች ፍቃድ ለመስጠት ነው። ባለሥልጣኑ በስድስት ወር የእቅድ ክንውንም ለ1ሺ155 አልሚዎች ፈቃድ ሰጥቷል። አፈፃፀሙም 54 በመቶ ሆኖ ተመዝግቧል። ባለሥልጣኑ የተሰጡ ፍቃዶችንም የማስተዳደር ኃላፊነት ስላለበት ፍቃድ የወሰዱ አልሚዎች በአግባቡ ኃላፊነታቸውን መወጣታቸውን በመከታተል ውጤታማ የሆኑት ደግሞ እንዲቀጥሉ ያበረታታል። የፍቃድ እድሳትም ያከናውናል። በዚሁ መሠረትም የ144 አልሚዎችን ፈቃድ አድሷል። ምንም እንኳን ፍቃድ መሰረዝ በእቅድ የሚያዝ ተግባር ባይሆንም ወደ ልማቱ ያልገቡትን ፈቃዳቸውን በመሰረዝ ለቀጣይ ልማት ዝግጁ ማድረግ ግዴታ በመሆኑ ወደ እርምጃ ይገባል። ይህን ተግባር የሚወጣውም ለአልሚዎቹ ጊዜ ከሰጠ በኋላ ነው። በዚሁ መሠረትም በስድስት ወራት ጊዜ በባህላዊ የወርቅ ልማት የተሰማሩትን ጨምሮ በተለያየ የማዕድን ልማት ውስጥ የነበሩ 115 ፈቃዶችን ሰርዟል። ፍቃድ ከተሰረዘባቸው ውስጥ ሪፖርት ወይንም መረጃ የማያቀርቡ፣ እንዲሁም የከሰል ድንጋይ ልማት ላይ ለመሰማራት የጥናትና የምርት ፈቃድ ወስደው በስምምነታቸው መሠረት ወደ ሥራ



አቶ ተስፋዬ መገርሣ፤

ያልገቡ ይገኙበታል።

በማዕድንልማቱየተከናወኑትንሥራዎችናየተገኘውን ገቢ በተመለከተ አቶ ተስፋዬ እንዳስረዱት፤ ባለሥልጣኑ በተለይም ለውጭ ገበያ በሚቀርቡ የማዕድን ዓይነቶች ላይ ተልዕኮዎችን (ግቦችን) ይዞ ነው ወደ ሥራ የገባው። በወርቅ ማዕድን፣ ከጌጣጌጥ ማዕድናት ደግሞ ታንታለም ይጠቀሳሉ። በበጀት አመቱ በማህበራትና በኩባንያዎች በሚከናወን የማዕድን ልማት 5ሺ685 ኪሎ ግራም ወርቅ ለማምረት በእቅድ የያዘ ሲሆን፣ ከእቅዱ በስድስት ወር ውስጥ ተመርቶ ለብሔራዊ ባንክ የገባው የወርቅ መጠን አንድ ሺ561 ኪሎግራም ነው። አጠቃላይ ክንውኑ 27 ነጥብ 5 በመቶ ሆኖ ተመዝግቧል። ይህ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ የተመዘገበው ውጤት እጅግ የወረደ ሆኖ ነው የተገኘው። ዝቅተኛ አፈፃፀም ለመመዝገቡ ሕገወጥ ግብይትና ወርቅ አምራች በሆኑ የክልሉ አካባቢዎች እያጋጠመ ያለው የፀጥታ ችግሮች ዋነኛ ምክንያቶች መሆናቸውን ነው አቶ ተስፋዬ የሚያስረዱት። የክረምት ወቅት ለማዕድን ልማቱ ምቹ አለመሆንም ተጽእኖ እንዳለውና ይህም በጉጂ በሚከናወነው የደለል ወርቅ ልማት ሥራ እንደሚያጋጥም አመልክተዋል። በአሠራር የሚያጋጥሙ አንዳንድ ነገሮች (ቴክኒካል) በተመሳሳይ ጫና እንደሚያሳድር አስታውሰዋል።

መንግሥት ምንም እንኳን ባደረገው የ35 በመቶ የዋጋ ማሻሻያ መሠረት ከአልሚዎች ወርቅ እየገዛ ቢሆንም ወርቅ የሚቀበልበት ዋጋ ሕገወጥ ግብይትን ለመከላከል እንዳላስቻለው የጠቀሱት አቶ ተስፋዬ፤ ወርቅን ማንኛውም ሰው በቀላሉ ይዞ ለመጓጓዝ ምቹ ሁኔታ መኖሩም ክትትልና ቁጥጥሩን ፈታኝ እንዳደረገው አመልክተዋል። በተለይም የፀጥታ ሁኔታን ተገን በማድረግ የሕገወጥነቱ አደገኛነት እየከፋ የመጣ ቢሆንም መንግሥት የተለያዩ እርምጃዎችን በመውሰድ ሕገወጥነትን ለመከላከል ያልተቆጠበ ጥረት ማድረጉንም ገልጸዋል።

አቶ ተስፋዬ እንደሚያስረዱት፤ አምራቾች ምን ያህል እንደሚያመርቱ ከዚህ ቀደም እቅድ አልነበራቸውም። አመረትን ያሉትን ብቻ ነው ለብሔራዊ ባንክ ሲያቀርቡ የቆዩት። አሁን ላይ ግን በእቅድ እንዲመሩ ማድረግ የሚያስችል ሥርዓት በባለሥልጣኑ በኩል ተመቻችቷል። ባለስልጣኑ ይህን ሲያደርግም ለባህላዊ ወረቅ አምራቾች የሙያ ስልጠናና አስፈላጊ የሆኑ ድጋፎችን በማመቻቸት ነው። በዚህ መልኩ ምቹ ሁኔታ ከፈጠረ በኋላ በወር እስከ 200 ኪሎግራም ወርቅ ማምረት እንዳለባቸው ስምምነት ላይ በመድረስ ነው በበጀት አመቱ ወደ ሥራ የተገባው። አፈጻጸሙ ከማህበራት ማህበራት የሚለያይ ቢሆንም በእቅድ መንቀሳቀሱ ግን ውጤታማ እንደሚያደርግ ታምኖበታል። ለወርቅ ልማቱ የሚያግዝ ዘመናዊ መሣሪያ (ማሽን) የሚጠቀሙ፣ ከባህላዊ የወርቅ አምራቾች በተሻለ የሚያመርቱና የምርት አቅማቸውም ከፍ ያለ አነስተኛ የወርቅ አምራቾች ወይንም ልዩ አነስተኛ ባለፈቃዶችን ደግሞ በተለየ ሁኔታ ልማቱን እንዲያከናውኑ አድርጓል። አልሚዎችን ሁለት ቦታ በመከፈል በወር ሦስት ኪሎግራም የሚያመርቱ ሁለተኛ ደረጃ፣ በወር ደግሞ ወደ አራት ነጥብ ስምንት ኪሎግራም ማምረት የሚጠበቅባቸውን ግልጽ በማድረግ መግባባት ላይ ተደርሶ ነው ወደ ሥራ የተገባው።

በማዕድን ልማት ሥራ የተደረገውን ጥረትና የተገኘውን ውጤት የገለጹልን አቶ ተስፋዬ፤ ከጌጣጌጥ ማዕድን ዘርፍ አንዱ የሆነው የታንታለም ማዕድንም ለሕገወጥ ገበያ የተጋለጠና በስፋትም ወደ ጎረቤት አገራት እንደሚሻገር በተለያየ ጊዜ የሚወጡ መረጃዎች እንደሚያመለክቱ አንስተዋል። ከዚህ ቀደም በነበረው ተሞክሮ የታንታለም ማዕድን ወደ ማእከላዊ ገበያ የሚመጣበት ዕድል እንዳልነበረም አስታውሰዋል። ማዕድኑ በዓለም ገበያ ተፈላጊና በዋጋም ውድ ሆኖ ለአገር ኢኮኖሚ እድገት ጥቅም ሳያስገኝ የቆየ መሆኑንም ጠቅሰዋል። በዚህ በጀት አመት ግን በትኩረት ተሠርቶ ጥሩ ውጤት እንዲመዘገብ ተደርጓል ብለዋል። እርሳቸው እንዳሉት ከአምራች ማህበራት ጋር በተሠራው ሥራ ከዚህ በኋላ የታንታለም ማዕድን ወደ ማዕከላዊ የሚመጣበት ሁኔታ ተመቻችቷል። በአሠራር ላይም ለውጥ ለማምጣት በተከናወነው ተግባር የታንታለም ማዕድን ጥራትን ለማረጋገጥ በግለሰብ ይከናወን የነበረውን ወደ ውጭ አገር የመላክ የአሠራር ሂደት ተሻሽሏል።

እንደ ክልል ለዓለም ገበያ ቀርበው ከተለዩ ማዕድኖች የውጭ ምንዛሪ ገቢ ለማስገኘት በበጀት አመቱ በእቅድ ከተያዘው 394 ሚሊዮን ዶላር በስድስት ወር 127 ነጥብ 5 ሚሊዮን ዶላር መገኘቱን የተናገሩት አቶ ተስፋዬ፤ በአገር ውስጥ በተከናወነ ግብይት ደግሞ ወደ 400 ሚሊዮን ብር (አራት መቶ ሚሊዮን ብር) ገቢ ለማግኘት ከተያዘው እቅድ ወደ 243 ሚሊዮን ብር በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ መሰብሰብ ተችሏል። በማዕድን ልማቱ በተለይም በወርቅ የተገኘው ውጤት ከፍ ያለ ባይሆንም በተለያየ ተግዳሮት ውስጥ አልፎ የተከናወነ በመሆኑ አበረታች እንደሆነም ተናግረዋል።

በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወጪ ከውጭ ተገዝተው የሚገቡ ለግንባታና ለኢንዱስትሪ ግብአት የሚውሉ የማዕድን ውጤቶችን በአገር ውስጥ በመተካት ረገድ ተጠቃሽ ተግባር መከናወኑን አቶ ተስፋዬ አስረድተው፤ ለአብነትም ለሲሚንቶ አምራች ኢንዱስትሪዎች ለኃይል ግብአትነት የሚውለውን የድንጋይ ከሰል በአገር ውስጥ ለማቅረብ እንዲቻል አልሚ ኩባንያዎች በዘርፉ እንዲሰማሩ በተሠራው ሥራ የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪዎች ጭምር ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሁኔታ መፍጠር መቻሉን አንስተዋል።

ባለሥልጣኑ በማዕድን ልማቱ ከ160ሺ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ከያዘው አመታዊ እቅዱ፤ በስድስት ወራት ጊዜ ለ54ሺ760 የሥራ ዕድል መፍጠሩን አቶ ተስፋዬ አመልክተዋል። ባለሥልጣኑ ከማዕድን ልማቱ ጋር ተያይዞ የሚነሳውን የአካባቢ ተጽእኖና ከልማቱ ቱርፋት የመጠቀም ሁኔታንም በእቅዱ ማካተቱንና በዚህ ረገድም የተለያዩ ተግባራት መከናወናቸውን አመልክተዋል።

እንደርሳቸው ማብራሪያ ለማዕድን ልማት ተብሎ ቁፋሮ የሚከናወንባቸው አካባቢዎችን መልሶ ማልማት አንዱ ተግባር በመሆኑ አንድ ማዕድን አልሚ ፍቃድ ከመውሰዱ በፊት የአካባቢና ማህበራዊ ተጽእኖዎች ላይ የሚሠራቸውን ሥራዎች በሰነድ አስደግፎ ማቅረብ እንዳለበት ቀድሞ እንዲያውቅ ይደረጋል። ከዚህ ቀደም ለማዕድን ልማት ተቆፍረው ያለሙ መኖራቸውንና በዚህ በጀት አመት 407 ሄክታር መሬት ለማልማት በባለስልጣኑ መታቀዱንና ከዚህ ውስጥም 189 ሄክታር በማልማት ወደነበረበት መመለስ መቻሉን ገልጸዋል። መሬቱን መልሶ ከማልማት በተጨማሪ ከአጠቃላይ ከማዕድን ፕሮጀክት ተሰብስቦ ለአካባቢው ማህበረሰብ ልማት የሚውል የማህበረሰብ ፈንድ አለ። የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቶም ሕጋዊ ፈቃድ ወስዶ በልማቱ የተሰማራ አልሚ ከአጠቃላይ ልማቱ ከሚያገኘው ትርፍ ሁለት በመቶ ለልማቱ እንዲያውል እንደሚደረግ አስረድተዋል። በዚህ መንገድ ከአልሚው የተሰበሰበው የማህበረሰቡን ፍላጎት መሠረት ያደረገ ልማት እንደሚከናወንበትም ተናግረዋል። እንዲህ ያለው አሠራር ከዚህ ቀደም የተለመደ እንዳልነበር ጠቅሰዋል።

እንደ አቶ ተስፋዬ፤ የማዕድን ልማት የአካባቢ ማህበረሰብ፣ የፀጥታ ኃይልና የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ያላሰለሰ ድጋፍና አጋርነት ይጠይቃል። ቅንጅታዊ አሠራሩ የሠመረ ሲሆን፣ የላቀ ውጤት ይመዘገባል። በዚህ መንገድ የሚከናወን የማዕድን ልማት በአልሚውና በአካባቢው ማህበረሰብ መካከል መልካም ግንኙነት እንዲፈጠር ያደርጋል። መልካም ግንኙነቱ ደግሞ ማህበረሰቡ ልማቱን እንዲደግፍና ኃላፊነትም እንዲሰማው ያስችላል።

በስድስት ወር ውስጥ የታየው አፈፃፀም ለቀሪው ጊዜ ምን መሠረት ይጥላል? ወደ ልማት ያልገቡት አልሚዎችን ፍቃድ መሰረዝ ጉዳይ ተደጋግሞ የሚነሳ በመሆኑ ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት ትክክለኛ አልሚ በመለየት ላይ ትኩረት መስጠት አይሻልም ወይ? በሚል ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች አቶ ተስፋዬ ሲመልሱ፤ በስድስት ወር ክንውን ተንጠባጥበው የቀሩ ሥራዎችና በቀጣይ ስድስት ወራት ለመሥራት በእቅድ የተያዙትን ደምሮ መሥራት ይጠበቃል። ሥራዎችን በመፈተሽ በተሻለ ሁኔታ ለመንቀሳቀስ ነው ባለሥልጣኑ የተዘጋጀው። ከመንግሥትና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋርም በቅንጅት በሚሠራው ላይም ትኩረት ይደረጋል። ከፍቃድ አሰጣጥ ጋር ተያይዞ ለተነሳውም አልሚው ፍላጎትና ገንዘብ ስላለው ብቻ ሳይሆን፣ በዘርፉ በቂ እውቀት እንዳለውም የሚያቀርበውን ሰነድ መነሻ በማድረግ በጥንቃቄ ማየትና ግንዛቤም መፍጠር እንደሚያስፈልግ ካለፉ አሠራሮች ትምህርት በመውሰድ መሥራት እንዳለበትም ግንዛቤ በመያዙ በዚህ መንገድ በመሥራት ክፍተቱን ለመፍታት ጥረት ይደረጋል ብለዋል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## የሀሳብ ገጾች

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ዘንቦ አባርቷል..። ስስ ለጋ ፀሐይ በምሥራቅ አድማስ ላይ አቅላልታለች። እንዲህ ሲሆን ደስ ይለዋል..እንዲህ ሲሆን መኖር ያረካዋል። በዘነበ ሰማይ ላይ ያቅላላች እንቡጥ ፀሐይ ሲመለከት..በተሲያት አለም ላይ ሊዘንብ ያለ ጉሩምሩምታ ሲያደምጥ ተፈጥሮና ፈጣሪ በአንድ ላይ የወገኑ ይመስለዋል። የተፈጥሮ የሀቅ ሚዛን ፍንትው ብሎ ይታየዋል..ከሀሳቡ የጠፋው የእግዜር መለኮታዊ ኃይል ህላዊ ያገኛል። ተፈጥሮ ያስደንቀዋል..የሕይወቱ አንድና ብቸኛ እውነት ተፈጥሮ ነው። በተፈጥሮ ውስጥ ማን እንዳለ ግን አያውቅም። እግዜር ይሆን ሳይንስ፣ አዳም ይሁን ዳሪውን ዛሬም ድረስ አልደረሰበትም። እግዜር የለም ባለ ማግስት ለእሱ ጥያቄ መልስ ይመስል ልክ እንዲህ እንደአሁኑ ተፈጥሮና እውነቷ በአንድ ወግነው ሰማይ ርቃን ላይ ይታዩታል። በሚያሳምን እውነት፣ በሚገርም ልዕልና ሙልዐተ አለሙ ላይ ተስለው የፈጣሪን መኖር ይነግሩታል። ይገርመዋል የተፈጥሮ እውነት..

ቡና ይወዳል። ጠቆር መረር ያለ ቡና ነፍሱ ነው። ማለዳውን በትኩስ ቡና መጀመር ሊተወው ያልቻለ የዘወትር ልማዱ ነው። በተለይ እንዲህ እንደ አሁኑ እግዜርና ተፈጥሮን በአንድ ላይ ሲያገኛቸው.. በተለይ እንዲህ እንደ አሁኑ መኖር በሚያስናፍቅ እውነት ውስጥ ሲሆን.. በተለይ እንዲህ እንደ አሁኑ ዘንቦ ባባራ አባርቶ በፈካ ፀሐይና ዝናብ በተጋቡበት የልጅነት እውነቱ ውስጥ ሲሆን ጥቁር ትኩስ ቡና መጠጣት ልዩ ስሜትን ይሰጠዋል።

ከነጥያቄው ወደ አንድ ካፌ አመራ።

እንደ እሱ በትኩስ ቁርስና በትኩስ ቡና የሚዝናኑ ጥንድና ነጠላ ሰዎች ካፌውን ሞልተውታል። የሰው ልጅ የሚኖረው ለሆዱ ነው። ሆድ ባይኖር የሰው ልጅ ምድራዊ ዕጣ ፈንታ ምን ይሆን ነበር የሚለውን ለመመለስ ብዙ ለፍቶ አልተሳካለትም። የሰው ልጅ ከመብላትና ከመጠጣት የተለቀ ሌላ ትልቅ ጉዳይ እንደሌለው ሲያስብ ሰው መሆን ትርጉም ያጣበታል። እሱ ራሱ እንኳን በጠዋት የሚነሳው ትኩስ መራራ ቡና ለመጠጣት ነው። ሰውነት ከመብላትና ከመጠጣት የላቀ እውነት ቢኖረው ደስ ይለው ነበር ግን እስካሁን እዛ እውነት ላይ አልደረሰም። አካባቢውን ለመቃኘት ዕድል ሳትሰጠው አንድ ጠይም አስተናጋጅ ፊቱ ቆመች።

ትኩስ ጥቁር መራራ ቡና እንደሚፈልግ ነግሮ ከፊቱ አሸሻት።

የአስተናጋጇን ከአይኑ መሸሽ ተከትሎ ወደ ተወው ሀሳቡ ተመለሰ። ብዙ ነገር ያስገርመዋል። ብዙ ነገሮች ጥያቄ ይፈጥሩበታል። ይሄ ዓለም የማን እንደሆነ እስካሁን አልገባውም። እግዜርም ሳይንስም የየራሳቸውን እውነት ይዘው ሊያስረዱት ሞክረዋል። ዛሬም ድረስ ግን እውነቱ ላይ አልደረሰም። እግዜርና ሳይንስ ከልጅነቱ ጀምሮ ግራ ሲያጋቡት የመጡ ያልተመለሱ ጥያቄዎቹ ናቸው። በልጅነቱ የሚያውቃቸው የአባቱ ነፍስ አባት የሰው ልጅ በፈጣሪ አምሳል እንደተፈጠረ ነግረውት ነበር። የሰፈራቸው የአጥቢያ ገበዝ አባ ዳምጤ ‹በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ ብለው ለሕዝቡ ሲሰብኩ አድምጧል። ትምህርት በጀመረበት ጥቂት አመት ውስጥ ዛሬም ድረስ የማይረሳው ሳይንስ አስተማሪያቸው አንገቱ ላይ ያደረገውን ትልቅ የጎለጎታ መስቀል በእጁ እየነካካ የሰው ልጅ ከዝንጀሮ ነው የመጣው ሲል አስተምሯቸው ነበር። በነጋታው እኔና እናንተ የዝንጀሮ ትውልዶች ነን..በዝግመተ ለውጥ ነው ከዝንጀሮነት ወደ ሰውነት የተቀየርነው ሲል በሰው ልጅ ህላዊ ውስጥ ከፈጣሪ ይልቅ ሳይንስ እውነት እንዳለው በልበ ሙሉነት አስረግጦ አስተምሯቸው ነበር። ያን ቀን በእየሱስ የሚያምን..አንገቱ ላይ ትልቅ የጎለጎታ መስቀል ያደረገ አንድ አስተማሪ የአባን እውነት ሻረበት። ያ መምህር መስቀሉን ለምን እንዳደረገው ግን ዛሬም ድረስ አልገባውም። ሳይንስና እግዜር የተጋጩበት ያኔ ነበር። ሳይንስን እየተማሩ እየሱስን መከተል.. ለዳሪውን እውነት እየተገዙ የፈጣሪን መኖር መመስከር እንደምን ይቻላል? ትናንትም ዛሬም ያልገባው ጥያቄው ነው። ማንም ያልመለሰለት የልጅነትና የወጣትነት ጥያቄው። ዛሬም ድረስ በዚህ ያልተመለሰ ጥያቄው ውስጥ ይኖራል። እሱ ብቻ አይደለም አጠቃላይ ዓለም በዚህ ያልተመለሰ ጥያቄ ውስጥ ትመስለዋለች። አጠቃላይ የሰው ልጅ በዚህ ዝቅታና ከፍታ ውስጥ ነው ብሎ ያምናል። ዓለም የማናት? እሱስ የማን ነው? የፈጣሪ ወይስ የተፈጣሪ?..የሳይንስ ወይስ የረቂቅ እውነት? አልገባውም። ሌላ ያልተደረሰበት እውነት ያለ ይመስለዋል። የሌለም ይመስለዋል። አልታወቀውም እንጂ የሰው ልጅ ዛሬም ድረስ ባኦት አምላኪ ነው። ዛሬም ድረስ ለሁለት ጌታ የሚገዛ ነው። ዛሬም ድረስ ቄሳርን የሚያመልክ ነው።

ብዙዎቹ መረረ.. ቀጠነ..ስኳር አነሰው..ስኳር በዛው እያሉ የሚያማርሩና የሚያመናጭቁ ምስጋና የለሽ ናቸው።

ትኩስ ጥቁር መራራ ቡና መጣለት። ፈገግ አለ..አንድ መዐት ፈገግታ።

ከነፈገግታው ወደ ጠይሟ ሴት ቀና አለ። እንደ መልኳ ጠይም ቡና ታመጣልኛለች ብሎ ጠብቆ ነበር። ትዕዛዙን አንዱንም ሳታጎድል ስላመጣችለት በፈገግታ እጅ ነሳት።

ጠይሟ አስተናጋጅ ግራ መጋባት ተፈጠረባት። ማንም ሰው ቡና አዟት እንዲህ እንደእሱ ደስ ሲለው አይታ አታውቅም። ብዙዎቹ መረረ..ቀጠነ..ስኳር አነሰው.. ስኳር በዛው እያሉ የሚያማርሩና የሚያመናጭቁ ምስጋና የለሽ ናቸው። በትንሽ ነገር አመስጋኝና ደስታን የሚያገኝ ሰው ብርቋ ነው። የተቀዳ ቡና ስሰጠው እንዲህ የሆነ ቡና አፍልቼ ባጠጣው ምን ሊሆን ነበር ስትል እያሰበች ከአጠገቡ ሄደች።

በዘነበ ሰማይ ባቅላላች ጀምበር ስር ሆኖ..በፈጣሪና በተፈጥሮ እውነት ውስጥ ተጠልሎ የሚወደውን ቡና ፉት አለ። ቡናው ወደ ሆዱ ሲወርድ ፍጹም በሆነ ደስታ ነበር። ይሄስ የሰውነት ደስታ የማነው? ደስታ ፈጣሪው ማነው? መነሻና መድረሻውስ? ከቡናው ጋር ሌላ ጥያቄ መጣበት።

ለምንድነው የሚጠይቀው? ለምንድነው ጠይቆ መልስ የማያገኘው? ያልደረሰበት የእውነት ስፍራ ያለ ይመስለዋል። ወይም ደግሞ ከእውነቱ ጋር እየኖረ ሆድና ጀርባ ሆኖ እንዲህም ይመስለዋል።

ከቡናው ፉት አለ..የቡናውን ስኒ ጠረጴዛው ላይ ከማስቀመጡ ሰማይ ማጉረምረም ጀመረ። ወደ እውነቱ እየተጠጋ መሰለው። በዘነበ ሰማይ ርቃን ላይ ፍንትው ያለችው ለጋ ፀሐይ በዳመና ድባቅ ተመታ ብኩርናዋን አጣች። ፀሐይ ገብታ ካፊያ መጣ። ሌላ ሰማይና ምድር ተፈጠረ። ተፈጥሮ ከፈጣሪዋ ጋር በትልቅ ሰማይ ላይ ተስለው አየ። ይሄ እውነት የማነው?

ለመጨረሻ ጊዜ የቡናውን ስኒ ወደ አፉ አለ....ቡናው ወደ ሆዱ ሲወርድ ጥያቄዎቹን እየመለሰለት ነበር።

በፀሐይ ላይ ዝናብ..በዝናብ ላይ ፀሐይ። እውነቱ ጥጋ ጋ ደረሰ። ከሚፈልገው..ከሚያስፈልገውም ሀቅ ጋር ተገናኘ። ፈጣሪ ከሚለው እውነት ጋር።

# ዓለም አቀፍ



## አሜሪካ ቀዩን መስመር አልፋለች ስትል ሰሜን ኮሪያ ገለጸች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- አሜሪካ በኮሪያ ልሳነ ምድር የምታደርገው ወታደራዊ እንቅስቃሴ ቀጣናውን ወደለየለት ጦርነት ውስጥ ሊከተው ይችላል ስትል ሰሜን ኮሪያ አስጠነቀቀች።

የአገሪቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባወጣው መግለጫ፣ አሜሪካ ከደቡብ ኮሪያ ጋር እያደረገች ያለችው ወታደራዊ ልምምድ «ቀይ መስመሩን ያለፈ» ነው ብሎታል።

የኮሪያ ልሳነ ምድርን ዋነኛ የጦር ቀጣና ለማድረግ የሚካሄደውን እንቅስቃሴም ተቃውሟል።

የአሜሪካ እና ደቡብ ኮሪያ የጦር አውሮፕላኖች በትናንትናው ዕለት ግዙፍ ወታደራዊ ልምምድ አድርገዋል። ይህን ልምምድም ጸብ አጫሪነት ነው ብላ የምታምነው ፒዮንግያንግ፣ አስፈላጊ ከሆነ የኒዩክሌር የጦር መሣሪያዎቼን ተጠቅሜ አጸፋውን እመልሳለሁ በሚል ዝታለች።

ዋሽንግተን ቀጣናውን ከሚያተራምስ እርምጃዋ እስካልታቀበች ድረስም ኮሪያ ለንግግር ዝግጁ እንደማትሆን ነው የአገሪቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በመግለጫው ያመላከተው። ዋይትሃውስ በበኩሉ «ከፒዮንግያንግ ጋር ግጭት የሚፈጥር ድርጊት አልፈጸምንም፤ አሁንም የምንሻው ዲፕሎማሲያዊ መፍትሄን ነው» ብሏል።

«የሰሜን ኮሪያን የኒዩክሌር ጦር መሣሪያ ልማት ለመግታት በጸጥታው ምክር ቤት የተላለፉ ውሳኔዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ግን ከአጋሮቻችን ጋር መሥራታችንን እንቀጥላለን» የሚል መግለጫንም አውጥቷል።

የአሜሪካ የመከላከያ ሚኒስትር ሊዩድ ኦስቲን በዚህ ሳምንት በደቡብ ኮሪያ ባደረጉት ጉብኝትም ማጠናከራቸው የሚታወስ ሲሆን ሁለቱ አገራት የሰሜን ኮሪያን የኒዩክሌር ግስጋሴ ለማስቆም ወታደራዊ አጋርነታቸውን ማጥበቃቸው ፒዮንግያንግን አስቆጥቷል።

ቁጣዋንም ባለፈው ዓመት ብቻ ከ60 በላይ የሚሳኤል ሙከራዎችን በማድረግ መግለጿን ነው ሬውተርስ ያስታወሰው።

ከ28 ሺህ በላይ የአሜሪካ ወታደሮች የሚገኙባትና ከዋሽንግተን «ኒዩክሌር እናስታጥቅሻለን» በማለት ቃል የተገባላት ደቡብ ኮሪያ ግን ለጎረቤቷ ዛቻና ወቀሳ ምላሽ አልሰጠችም።

## በታኅሣሥ ወር ብቻ 2 ቢሊዮን የዓለም ሕዝብ በየቀኑ ፌስቡክ ተጠቅሟል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



ማርክ ዙከርበርግ

አዲስ አበባ፡- በታኅሣሥ ወር ብቻ በየቀኑ ፌስቡክን የሚጠቀመው የዓለም ሕዝብ ቁጥር በአማካይ 2 ቢሊዮን መድረሱን ቢ ቢ ሲ ዘግቧል።

ይህ ከፍተኛ የተጠቃሚዎች ቁጥር የፌስቡክ ባለቤት የሆነው ሜታ ኩባንያን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከደረሰበት የፋይናንስ ቀውስ ሊታደገው ይችላል ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን፣ ኩባንያው ካለፈው የፈረንጆች ዓመት ወዲህ የማስታወቂያ ገቢው እየቀነሰ ጠቅላላ ኩባንያውን ለማስተዳደር የሚያወጣው ወጪ ደግሞ እየጨመረ መጠነኛ ችግር ውስጥ ገብቶ እንደነበር ይታወሳል።

ይሁንና መሥራቹ ማርክ ዙከርበርግ “2023 ውጤታማ ዓመት ይሆናል” ብሎ መናገሩን ተከትሎ የሜታ ኩባንያ የአክሲዮን ገበያ ሽያጩ ከፍ ማለቱንና አሁን ላይ እሱና ኩባንያው ወጪ በመቀነስ ላይ ከፍተኛ ትኩረት ያደርጋል ተብሏል።

ሜታ ኩባንያ ከፌስቡክ ሌላ ኢንስታግራምን እና ዋትስአፕን በባለቤትነት የሚያስተዳድር ሲሆን፤ ባለፈው የፈረንጆች ዓመት ይህ ኩባንያ ወጪውን ለመቀየር መዋቅሩን በማስተካከል 11 ሺህ ሠራተኞችን ከሥራ አሰናብቷል። ይህም ከጠቅላላ የሠራተኛ ቁጥሩ 13 እጁን ይይዛል።

ሜታ ባለፈው ዓመት የፌስቡክ ተጠቃሚዎች ቁጥር ባልተጠበቀ ሁኔታ እየቀነሰብኝ ነው ሲል ለሸሪኮቹ እንድታውቁት የሚል መልዕክት ልኮ የነበረ ሲሆን፤ ይህ የተጠቃሚዎች ቁጥር መቀነስ በፌስቡክ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የተከሰተ ነበር።

ይህን ተከትሎ ኩባንያው የኢንቨስትመንት ትኩረቱን ምናባዊ እውነታ ላይ እንደሚያደርግም ጠቁሞ ነበር። ይሁንና ባለፈው ታኅሣሥ ወር ላይ ዕለታዊ የፌስቡክ ተጠቃሚዎች ቁጥር በአራት እጅ ጨምሮ ታይቷል።

ዙከርበግር እንደሚለው ኩባንያው ሪል የተሰኘው አጫጭር ቪዲዮ የሚያጋራበት በደንበኞቹ ዘንድ እየተወደደለት መጥቷል። ይህ በተለይ በወጣቶች ዘንድ ይበልጥ የሚመረጥ ቲክቶክን የመሰለ የማኅበራዊ ትስስር አንድ መንገድ ነው።

ይህ ከቲክቶክ ጋር የሚመሳሰለው ሪል ተጠቃሚዎችን እያበዛለት እና ዶላርም እያስገባለት እንደሆነ ኩባንያው ተናግሯል። ሜታ ባለፉት ዓመታት መንገጫገጩን ተከትሎ ገበያ ያጡ ድርሻዎችን ከድርሻ ገበያ 40 ቢሊዮን ዶላር አውጥቶ መልሶ እንደሚገዛቸውም አስታውቋል።

# ስፖርት





## አድሜ ያጭበረበሩ አትሌቶች ላይ እርምጃ ተወሰደ

ብርሃን ፈይሳ

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በአሰላ እያካሄደ ባለው የወጣቶች ቻምፒዮና የእድሜ ተገቢነትን ያላከበሩ አትሌቶች ላይ እርምጃ ወሰደ። ፌዴሬሽኑ በዚህ ጉዳይ ላይ ጠንካራ አቋም ይዞ እየሰራ መሆኑንም አስታውቋል።

የኢትዮጵያ ከ20 ዓመት በታች ቻምፒዮና ለ11ኛ ጊዜ በአሰላ አረንጓዴው ስታዲየም በመካሄድ ላይ ይገኛል። በዚህ ውድድር ላይም ተሳታፊ መሆን የሚችሉት እድሜያቸው እስከ 19 ድረስ ያሉ አትሌቶች ብቻ ሲሆኑ፤ ይህን ጥሰው በተገኙት ላይም እርምጃ ወስዷል። እርምጃው የተወሰደባቸው 99 አትሌቶች ሲሆኑ፤ አትሌቶቹ በተለያዩ ውድድሮች ላይ በ2009፣ 2010 እና 2011 ዓ.ም በዚሁ ውድድር ላይ ተሳትፈው የነበሩ ናቸው። በፌዴሬሽኑ በኩል የተደረገው ይኸው ማጣራትም በሰነድ እንዲሁም በህክምና እይታ መሆኑን ፌዴሬሽኑ አስታውቋል። በመሆኑም እነዚህ አትሌቶች ከዚህ ውድድር የተሰረዙ መሆኑን ፌዴሬሽኑ ባወጣው ማስታወቂያ ጠቁሟል።

የእድሜ ገደብ በተደረገባቸው የአትሌቲክስ ውድድሮች ላይ የእድሜ ተገቢነት ችግር በተደጋጋሚ የሚስተዋል መሆኑ ይታወቃል። ችግሩ ከአገር ውስጥ ውድድሮች አልፎም በዓለም አቀፍ ቻምፒዮናዎች ላይም ስለሚንጸባረቅ በተደጋጋሚ አገሪቷን ትዝብት ላይ ሲጥላት ቆይቷል። ይህ ሁኔታም በተለይ በትክክለኛ እድሜያቸው ወደ ስፖርቱ የገቡ ታዳጊዎችን ዕድል የሚዘጋ በመሆኑ እንዲሁም እንደ አገርም በእድሜ ማጭበርበር የሥነምግባር ጉድለት እየሰፋ በመምጣቱ ፌዴሬሽኑ እርምጃ ወደ መውሰድ አቅንቷል።

በዚህም በቅርቡ በተካሄደው የፌዴሬሽኑ 26ኛው መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ በእድሜ ረገድ ቁርጠኛ አቋም ይዞ አስፈላጊውን እርምጃ እንደሚወስድ ከውሳኔ ላይ መድረሱ የሚታወስ ነው። በዚህም መሰረት ከውድድሩ መጀመር አስቀድሞም ፌዴሬሽኑ፤ እድሜያቸው 20 እና ከዚያ በላይ የሆናቸውን አትሌቶች ማሳተፍ ከፍተኛ የአትሌቲክስ ሕግ ጥሰት ስለሚሆን የትኛውም አሳታፊ አካል በእድሜ ተገቢነት ዙሪያ ከፍተኛ ትኩረት አድርጎ ለውድድሩ መቅረብ እንደሚገባ አስታውቆ ነበር።

ነገር ግን ክልሎች፣ ከተማ አስተዳደሮች፣ ክለቦች፣ የማሰልጠኛ ተቋማትና አትሌቶች ከዚህ ተግባራቸው እንዳልታቀቡ በዚህ ቻምፒዮና ተረጋግጧል። በመሆኑም አትሌቶቹን ለይቶ በማውጣት ከውድድሩ ሰርዟቸዋል። በቀጣይም ይህንኑ ስራ አጠናክሮ በመቀጠል ተመጣጣኝ እርምጃ እንደሚወስድም ነው ፌዴሬሽኑ ያሳሰበው።



## ደራርቱ ቱሉ በኢጋድ እውቅና ተሰጣት

ብርሃን ፈይሳ

የምስራቅ አፍሪካ በይነ መንግሥታት (ኢጋድ) ለምክትል ኮሚሽነር ደራርቱ ቱሉ እውቅና ሰጠ። ደራቱ እውቅናው የተሰጣት ለሰላም ላበረከተችው አስተዋጽኦ መሆኑም ተገልጿል።

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንን በፕሬዚዳንትነት እየመራች የምትገኘው አንጋፋዋ አትሌት ምክትል ኮሚሽነር ጄነራል ደራርቱ ቱሉ በኢጋድ እውቅና የተሰጣት ተፅዕኖ ፈጣሪ በመሆና ነው። ደራርቱ እውቅናው የተሰጣት የምስራቅ አፍሪካ በይነ መንግሥታት (ኢጋድ) በኬንያ ሞምባሳ ዓመታዊ ሪፖርቱን ለሶስተኛ ጊዜ እየገመገመ ባለበት ወቅት ነው። በመድረኩ ላይ ከሚካሄዱ መርሃግብሮች መካከል አንዱ መልካም አበርክቶ ላላቸው ግለሰቦች እውቅና መስጠት ሲሆን፤ ከድርጅቱ አባል አገራት መስፈርቱን ላሟሉት ይሰጣል።

በመልካም ምግባሯ የምትታወቀው ደራርቱ ቱሉም እውቅናውን እንድታገኝ ምክንያት የሆነው በኢትዮጵያ የሰላም ድምጽ በመሆን ባበረከተችው አስተዋጽኦ ነው። በቀጠናው በአየር ንብረት ለውጥ፣ አደጋ መከላከል፣ ሰላምና መረጋጋት፣ ሰብዓዊ እርዳታና በሌሎች ጉዳዮች የጎላ አበርክቶ የነበራቸው 21 ግለሰቦች እውቅናውን አግኝተዋል። ደራቱም በሰሜን ኢትዮጵያ የተከሰተውን ግጭት ተከትሎ ሰላም እንዲሰፍን በተደጋጋሚ በተለያዩ መድረኮች ድምጽ በመሆን ባበረከተችው በጎ ተግባር እውቅናው ተበርክቶላታል። ደራርቱም በቦታው በአካል በመገኘት እውቅናውን ወስዳለች።

በመድረኩ ላይ ጀግናው አትሌት ሻለቃ ኃይሌ ገብረስላሴ እንዲሁም ፕሮፌሰር አህመድ ዘካሪያ እውቅናውን ያገኙ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ናቸው።


# የጨረታ ማስታወቂያ

በጋምቤላ ክልል ትምህርት ቢሮ በ GEQIP_ E ድጋፍ በ2015 ዓ/ም በጀት ዘመን

**አንድ ሞንተሶሪ** በግልፅ ጨረታ ተጫራቾችን አወዳድሮ ለማሰራ ይፈልጋል፡፡

1. የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያለው፣
2. የምዝገባ ሠርተፊኬት ማቅረብ የሚችል፣
3. የአቅራቢነት የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችል፣
4. ተጨማሪ እሴት ታክስ (ቫት) ተመዝጋቢ የሆነ፣
5. 2015 ዓ/ም ከውዝፍ ግብር ነፃ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል፡፡
6. ተጫራቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ15 (አስራ አምስት) ተከታታይ ቀናት የማይመለስ ብር 200.00 (ሁለት መቶ ብር) በመክፈል የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ ዘውትር በስራ ሰዓት ቢሮ ቁጥር 20 በማቅረብ መግዛት ይችላሉ፡፡
7. ተጫራቾች የጨረታውን ዋስትና ማስከበሪያ 1% በሲፒኦ ወይም ጋራንቲ ብቻ ከጨረታ ሰነዶቻቸው ጋር አያይዘው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
8. ተጫራቾች የጨረታውን ዶክመንት ዋጋ ዋናውንና ኮፒ ሁለት (2) ለየብቻ በስም በታሸገ ኤንቪሎፕ በማድረግ ምዝገባ በ16ኛው የሥራ ቀን ከጠዋቱ 3:00 -3:30 ሰዓት ድረስ ለዚሁ በተዘጋጀው ሣጥን ውስጥ አስገብቶ በዚሁ ዕለት በ4፡00 ሰዓት ላይ ጨረታው ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ቦታ ይከፈታል፡፡ ቢሮው የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ስተጨማሪ ማብራሪያ በስልክ ቁጥር፡- 0475510136**

**የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ**

# የጨረታ ማስታወቂያ
# የጨረታ ቁጥር 001/2015

በጉለሌ/ክ/ከተማ ወረዳ 10 የጀኔራል ታደሰ ብሩ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ለ 2015 ለድጎማ በጀት አገልግሎት የሚውል ሎት 1 የጽሕፈት እና የትምህርት መሳሪያዎች እና ሎት 2 አላቂ የቢሮ ዕቃዎች በግልጽ ጨረታ አወደድሮ መግዛት ስለሚፈለግ ተጫራቾች ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን መስፈርት ማሟላት ይኖርባቸዋል፡፡

1. በዘርፉ የታደሰ ህጋዊ ንግድ ፈቃድ ያላቸው፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ መሆኑን አለባቸው፡፡ ተጫራቾች ይህንኑ የሚገልጽ ማስረጃ ዋናውንና ፎቶ ኮፒውን ይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም ሰነድ ለይ የሚሞላው ዋጋ ስርዝ ድልዝ መኖር የለበትም፡፡ ኮፒና ኦርጅናሉ ፖስታው ላይ መሃተም ፣ ፊረማ እና አድራሻ የሚገልጽ እና ስልክ ቁጥር ማስቀመጥ ይኖርባቸውል፡፡
2. ተጫራቾች የጨረታዉን ዝርዝር መግለጫ ሰነድ ጨረታው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ምዕራፍ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አጠገብ 50 ሜትር ከፍ ብሎ በሚገኘው በጉለሌ/ክ/ከተማ ወረዳ 10 የጀኔራል ታደሰ ብሩ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ቢሮ ቁጥር 202 የማይመለስ በየሎቱ ብር 100 (አንድ መቶ ብር ብቻ) በመክፈል ሰነዱን መውሰድ ይችላሉ፡፡
3. ተጫራቾች የሚያቀርቡትን እቃ ጥራት ያለው ደረጃውን የጠበቀ ስለመሆኑ ናሙና ማቅረብ ባለባቸው ናሙና ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
4. ተጫራቾች እቃዎችን ዝርዝር እና የጨረታ ማወዳደሪያ ሰነድ ላይ ስማችሁን በመጻፍ ፊርማችሁና አድራሻችሁን ማስፈርና ማህተም በማድረግ ማስታወቂያ ከወጣ ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ 10 የስራ ቀናት በጉለሌ/ክ/ከተማ ወረዳ 10 የምዕረፍ 2ኛ ደረጀ ት/ቤት አጠገብ በሚገኘው የጄኔራል ታደሰ ብሩ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ቢሮ ቁጥር 202 ለጨረታው በተዘጋጀ ሳጥን ውስጥ እስከ በ10ኛው ቀን 11፡00 ሰዓት ድረስ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
5. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ማስታወቂያው በወጣበት በ11ኛው ቀን በ 4:30 በጄኔራል ታደሰ ብሩ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ቢሮ ቁጥር 202 ይከፈታል፡፡ የጨረታው መከፈቻ ቀን ቅዳሜ እና እሁድ ወይም በዓል ቀን ከዋለ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተገለፀው ሰዓት ይከፈታል፡፡
6. ጨረታው ከተከፈተ በኃላ ተጫራቾች በሰነድ የሰጡት ዋጋ መለወጥ፣ መሻሻል ወይም ከውድድሩ እራሳቸውን ማግለል አይችሉም፡፡
7. የማወዳደሪያ ዋጋ ከቫት ጋር መጠቀስ አለበት፡፡
8. ተጫራቾች የጨረታው ማስከበሪያ ለሎት 1 ብር 1,000 (አንድ ሺህ ብር ብቻ) እና ለሎት 2 ብር 1,000 (አንድ ሺህ ብር ብቻ) በባንክ በተመሰከረለት CPO ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
9. መስሪያ ቤቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
10. ት/ቤቱ እንደ አስፈላጊነቱ የዕቃዉን ብዛት ከውል በፊት20% መጨመር ወይም መቀነስ ይችላል፡፡
11. አሸናፊ ድርጅት ዕቃዎቹን እስከ ጀኔራል ታደሰ ብሩ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ንብረት ክፍል በራሱ ትራንስፖርት አጠቃሎ ያስገባል፡፡

**ስተጨማሪ ማብራሪያ በስልክ ቁጥር፡-** 0989066757,+251118234865,+251118231128

**በጉለሌ/ክ/ከተማ ወረዳ10 የጄኔራል ታደሰ ብሩ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት**